



በማኅበረ ቅዱሳን የአሜሪካ ማዕከል ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ እየተዘጋጀ በየሚሶ ዓመቱ የሚወጣ የኤሌክትሮኒክስ መጽሔት

፯ኛ ዓመት ቁጥር ፫ ነሐሴ ፳፻፫ ዓ.ም.

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| የአሜሪካ ማዕከል መልእክት | 1 |
| ዜና | 2 |
| ስብከተ ወንጌል | 4 |
| ኪነ ጥበባት | 6 |
| የሐመረ ኖኅ እንግዳ | 7 |
| ለሕፃናት | 13 |


# የአሜሪካ ማዕከል መልእክት

## የፈተና ዓመት - የበረከት ዓመት

እንኳን ለ2004 ዓ.ም በሰላም እና በጤና አደረሳችሁ፣ አደረሰን፤ አምላከ ቅዱሳን እግዚአብሔር ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ በሰላም እና በጤና አሸጋገራችሁ አሸጋገረን እያለ አዲሱ ዓመት የበረከት እና የመልካም አገልግሎት ዓመት እንዲሆንልን በማኅበረ ቅዱሳን የአሜሪካ ማዕከል ስም መልካም ምኞታችንን እናቀርባለን። ለመጪው አዲስ ዓመት መልካም ምኞት የምናስተላልፈው አሮጌው ዓመት የፈተናና የብዙ በረከት እንደነበረም በማስታወስ ነው።

ብርሃነ ዓለም እያለች ቤተ ክርስቲያን በፍቅርና በቁልምጫ የምትጠራው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ሐዋርያዊ ቃል 2003 ዓ.ም. እንዴት እንዳለፈ የሚያሳይ ገላጭ ቃል ነው፤ እንዲህ ሲል፦ “መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን፣ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን” /ሮሜ. ፭፥፫-፬/።

ዓመቱ ማኅበራችን እንደወትሮው ሁሉ እንደወርቅ በእሳት-ፈተና ነጥሮ የወጣበት፣ አባላቱ በፈተናው ብዛት እና ክብደት መጠንም ብዙ በረከት ያገኘንበት በመሆኑ በመፈተናችን ያልተወንን እግዚአብሔርን የበለጠ እንድናመሰግንና ቸርነቱን እንድናውቅ ምክንያት ሆኖናል። በሐዋርያው አስቀድሞ እንደተባለው ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰብንም፤ ከአቅማችን በላይ እንፈተን ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ በመሆኑ በሚገጥመን ፈተና እንታገሥ ዘንድ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ አድርጎልናል፤ ያደርግልንማል። /፩ኛ ቆሮ. ፲፥፲፫/። ስለዚህም እናመሰግነዋለን።

የፈተናዎች መብዛት የማኅበራችን መንፈሳዊ አገልግሎት ትክክለኛ መሆኑን ከማሳየቱ በስተቀር ሌላ ነገር የለውም። በክርስትና ውስጥ ኖሮ፣ አማናዊቱን እምነት ይዞ፣ ስለ እምነቱ ቆሞ ነገር ግን ያልተፈተነ ማን ይገኛል? ራሱ ጌታችንም ቢሆን ተፈትኖ መፈተን እንዳለብን በተግባር አስተምሮናል። ሐዋርያው “እስመ ኢኮነ ሊቀ ካህናቲነ ዘኢይክል ሐሚመ ለድካምነ ዳእሙ ምኩር በኵሉ አምሳሊነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ፤ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም” /ዕብ. ፬፥፲፭/ ያለው ለዚህ ነው። መራራቱን የምናውቀው ለሚገጥመን ፈተና አንድም መታገሡን አንድም መውጫ መንገዱን በማመልከቱ ነው።

ይሁን እንጂ ጌታችን “ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ” እንዳለው /ሉቃ. ፳፪፥፴፩/ የጠላት ዲያብሎስ ፈተናዎች ብዙዎችን ከጸጋው ማዕድ፣ ከክብሩ አደባባይ ሊያርቁ፤ በቀቢጸ ተስፋ ጠምደው “ኑ እናንተ የአባቴ ቡሩካን” ከመስኘት ሊያጎድሉ ይችላሉ። በዚህ ዓይነቱ ወቅት እርስ በርስ ከመጽናናት ጋር የጀመሩትን መንፈሳዊ አገልግሎት የበለጠ ማጠንከር እና ለክብር ለመብቃት መጋደል ይገባል። ለዚህም አስቀድሞ በዚህች የተቀደሰች ሃይማኖት ያለፉትን በሙሉ በእዝነ ኅሊና መለስ ብሎ መመልከት፣ የተጋድሏቸውን አሰረ ፍኖት መከተል፣ በጽናትም እነርሱን መምሰል ያስፈልጋል። /ዕብ. ፲፪፥፫፣ ፲፫፥፯/።


ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ እስከ መወገር ድረስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁል እስከመሰቀል፣ ቅዱስ ጳውሎስ አንገቱን እስከመከለል፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሞቶ እስከመነሣት፣ ቅዱስ ቶማስ በቁሙ ቆዳውን እስከመገፈፍ ከሁሉም በላይ የነዚህ ሁሉ ሰማዕታት ፈጣሪ በመልዕልተ መስቀል እስከመሰቀል ድረስ ከታገሡ እኛ ለጊዜው የሚገጥመንን ጥቂት ፈተና ላለመታገሥ እና ላለማለፍ የሚያስችል ምክንያት አናገኝም።

በዘመናችን ምናልባት አጥንታችንን ለመንኮራኩር፣ ሥጋችንን ለአናብስት ለአራዊት፣ ወይም ለመቃጠል የሚሰጥ አይኖር

ይሆናል። ነገር ግን በተለያየ መንገድ አገልግሎታችንን እና ኑሯችንን በፈተና መንኮራኩር እየፈጩ፣ በእሳት እያቃጠሉ እና በተንኮል መስቀል እየሰቀሉ የሚፈልጉትን ለማግኘት የሚሞክሩ እንዳሉ በመረዳት ፈተናውን ከሰማዕትነት መቁጠር እና ራስን ለክብር ማጨት ይገባል።

በ2003 ዓ.ም. ይህንን እና ይህንን በመሳሰለው ፈተና ማለፋችን እውን ቢሆንም የአገልግሎቱ ፍሬ ደግሞ ጣፋጭ መሆኑን በዓይናችን እያየን፣ በጆሯችን እየሰማን ነው። በአሕዛብነት የኖሩ ብዙ ወገኖችን የወንጌልን ብርሃን እንዲያዩ መደረጉ፣ ገዳማት፣ አድባራት እና የአብነት ት/ቤቶች መሠራታዊ ርዳታ ለማግኘት መቻላቸው፣ ቤተ ክርስቲያናችንን ከውስጥ በመፈተን ምእመናንን ወደ ውጪ ለመግፋት ቀን ከሌሊት የሚተጉ የፕሮቴስታንታዊ የተሐድሶ መናፍቃንን ሥውር ዓላማ በማሳየት ኦርቶዶክሳውያን እንዲጠነቀቁ እና ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ መቻሉ፣ በማዕከላችን በተለያዩ አካባቢዎች የተጀመሩት አገልግሎቶች ተጠናክረው መቀጠላቸው ወዘተ በሙሉ ከፈተናው ጀርባ ያለ ትልቅ በረከት ነው።

ስለዚህ በዚህ በማዕከላችን ውስጥ የምትገኙ ቀጣና ማዕከላት እና አባላት በሙሉ ይህንን በመረዳት በአዲሱ ዓመትም የተጀመረውን ዓለም አቀፋዊ አገልግሎት የበለጠ በማጠናከር በኩል የሚጠበቅባችሁን የውዴታ ግዴታ ከመቼውም በበለጠ አጠንክራችሁ እንድትቀጥሉ እናሳስባለን። ጀምርን እንጂ አልፈጸምንም። ጥቂቷን አደረግን እንጂ ብዙ አልሰጠንም። በሁሉም ግን "የማንጠቅም ባሪያዎች ነን" እንላለን እንጂ ያደረግነውን በመመልከት ልንሠራው ከሚገባው ትልቅ ሥራ ወደኋላ አንልም። ለዚህም የቤተ ክርስቲያን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።




## ዜና

ምንጭ፡- የአሜሪካ ማዕከል የአባላትና
ቀጣና ማዕከላት ክትትል ክፍል

### ሐመርና ስምዐ ጽድቅን ለማሰራጨት የሚያስችል አዲስ አሠራር ተዘረጋ

የማዕከላት የልማት ተቋማት አስተዳደር የሐመር መጽሔትንና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን በቀጥታ ከኢትዮጵያ ለአባላትና ምዕመናን በአድራሻቸው ለመላክ የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት ዝግጅቱን አጠናቅቋል። ለዚህ አገልግሎት የሚውል ጽ/ቤት በዳላስ ከተማ፣ ቴክሳስ የተከፈተ ሲሆን የተቀላጠፈ የሥርጭትና የገቢ ማሰባሰብ ሥራዎችን ለመሥራት በውስን ሰዓት /part-time/ የሚያገለግል ሠራተኛ በመቅጠር በአዲሱ ዓመት የተጠናከረ አገልግሎት ለመስጠት አቅዷል። ቀጣና ማዕከላት የአባላትንና የደንበኞች አድራሻ በትክክል መዝግበው ወደ ክፍሉ በመላክ አገልግሎቱን እንደሚያጠናክሩ ይጠበቃል።

### "ዝክረ ጎርጎርዮስ" በሚል ርዕስ የስልክ ኮንፈረንስ መርሐ ግብር ተዘጋጀ

የአሜሪካ ማዕከል የትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕን ዕረፍት 21ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ "ዝክረ ጎርጎርዮስ" በሚል ርዕስ የብፁዕ አባታችንን የሕይወት ታሪክ፣ ያከናወኗቸውንና ሊያከናውኗቸው ይመኙ የነበሩትን ሥራዎች የሚያዘክር ሁለት ሰዓታት የወሰደ የስልክ ኮንፈረንስ መርሐ ግብር ሐምሌ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. አካሔደ። በዝግጅቱ የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ዜና ሕይወት የተደመጠ ሲሆን በዝዋይ ሐመረ ኖኅ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በብፁዕ አባታችን እግር ሥር ተቀምጠው ለመማር ዕድል ያገኙ፣ የሕይወት እና የአገልግሎት ፍሬዎቻቸውን በዓይናቸው ከተመለከቱት እና መጽሐፎቻቸውን በጥልቀት ካነበቡት አባቶች እና ወንድሞች ትዝታም ተደምጧል። በዝግጅቱ በርካታ አባላትና ምዕመናን ተሳትፈዋል።

### የሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋን በተመለከተ ጥናት ተዘጋጀ


"በዝርወት ባለች ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋ" በሚል ርዕስ በአሜሪካ ማዕከል የቅዱሳት መካናት ድጋፍና ሙያ አገልግሎት ክፍል ሥር በሚገኘው የጥናትና ምርምር ንዑስ ክፍል ጥናት ተካሔደ። ጥናቱ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ 16 ካህናት፣ በተለያዩ ስቴቶች የሚኖሩ 202 ወላጆች እና 168 ምዕመናን የተሳተፉበት ሲሆን የተገኘውም ውጤት በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ አሁን እየተሰጠ ያለው የሕጻናት ትምህርት የቤተ ክርስቲያንን ቋንቋ በመጠቀም በተጠናከረ ሁኔታ ቢሰጥ ቤተ ክርስቲያንን ወደ መጪው ትውልድ ለማሸጋገር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የሚያመላክት ሆኗል። በውጤቱ ላይ ውይይት እንዲደረግበትም በማኅበረ ቅዱሳን አሜሪካ ማዕከል የትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል ከሙያና ተራድኦ ክፍል ጋር በመሆን የስልክ ኮንፈረንስ መርሐ ግብር አዘጋጅቶ በሕጻናት ትምህርት ላይ እየሠሩ ያሉ፣ ዝንባሌውና ልምዱ ያላቸው አካላት እንዲሁም ወላጆችም እንዲሳተፉ ጋብዟል። የጥናቱን ዝርዝር ወደ

http://www.mahiberekidusan.org/portals/0/kids/kids education.pdf በመሔድ መመልከት ይቻላል።

## ማኅበረ በዓለ ወልድ 7ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን አካሔደ

ምንጭ:- ኀብተ ገብርኤል /ከዴንቨር/

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሰሜን አሜሪካ አህጉረ ስብከት ማኅበረ በዓለ ወልድ 7ኛ ዓመታዊ ጉባኤውን "ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ!" በሚል መሪ ቃል ከሐምሌ 23-24፣ 2003 ዓ.ም. በቺካጎ፣ ኢሊኖይ አካሔደ። በጉባኤው ላይ በሰሜን አሜሪካ የሦስቱ አህጉረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፣ ብፁዕ አቡነ አብርሃም እና ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፤ በተጨማሪም መልአከ ሕይወት አባ እስጢፋኖስ ባህሩ፣ መልአከ ሰላም ደጀኔ ሺፈራው፣ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት፣ በቺካጎ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የደብረ ገነት ቅድስት ድንግል ማርያም ካህናትና ዲያቆናት፣ የማኅበሩ አባላትና ጉባኤውን ለመካፈል የመጡ ወንድሞች እና እህቶች ተገኝተው ነበር። ዓርብ ሐምሌ 22 ቀን ከየስቴቱ የመጡት አባላትንና የጉባኤው ተካፋዮችን እግር በማጠብ እና የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት በማስተላለፍ አቀባበል ተደርጓል።



መርሐ ግብሩ በብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ትምህርት የተጀመረ ሲሆን ብፁዕነታቸው በቤተ ክርስቲያን ስለ ማኅበር አመሠራረት፣ ጥቅሙን እና ወደ ማኅበራት ሲገባ ምንን አውቆ መግባት እንደሚያስፈልግ ትምህርት ሰጥተዋል። "ቤተ ክርስቲያናቸንን እንዴት እንጠብቅ እኛስ እንዴት እንመላለስ" በሚል ርዕስ ላይም የቡድን ውይይት ተደርጓል። ጉባኤው ላይ በተገኙት የማኅበሩ አባላትና ጉባኤውን ለመካፈል በመጡ አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞች እና እህቶች ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታን አስመልክቶ የተነሱት ጥያቄዎች በብፁዓን አባቶች መልስ ተሰጥቶባቸዋል።

ማኅበሩ በ2003 የሠራቸው ሥራዎች በማኅበሩ ሰብሳቢ ለጠቅላላ ጉባኤው የቀረበ ሲሆን ማኅበሩ በቅርቡ የከፈተውን ድረ ገጽ /www.eotc-mbw.org/ ወደፊት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል። በተለይም በአሁኑ ሰዓት እየተባባሰ የመጣውን የተሐድሶ መናፍቃንን እንቅስቃሴ ለመካላከል የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ ከሚሠሩ አባቶች እና ማኅበራት ጋር እንደሚቆም አቋሙን አስታውቋል። በዚህ መሠረት የጉባኤውን መሪ ቃል "ንቁ፥ በሃማኖት ቁሙ!" በማለት ሰይሞ አባላቱ ቤተ ክርስቲያን ያለባትን ችግር እና በተሐድሶ መናፍቃን እየደረሰባት ያለውን ፈተና እንዲያውቁ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችንን መጠበቅ የሁላችንም ኃላፊነት መሆኑን እንዲረዱ አድርጓል።

በወቅታዊ "የቤተ ክርስቲያን ችግሮችና ፈተናዎች" ዙሪያም በዲ/ን ዳንኤል ክብረት ግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል። በቤተ ክርስቲያናቸን ያሉትን ችግሮችና ፈተናዎችን ለይቶ በማወቅ ነቅቶ ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ እንደሚያስፈልግ እና ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅ ተነግሯል። በመጨረሻም ብፁዓን አባቶች በሰጡት ቃለ ምዕዳን ሁሉም ቤተ ክርስቲያንን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበትና የጉባኤው ተሳታፊዎች በሁለቱ ቀናት ጉባኤ የተማሩትን ቃለ እግዚአብሔር በተግባር ሊያውሉ እንደሚገባ አሳስበው የመጪው ዓመት ጉባኤ በአትላንታ፣ ጆርጂያ እንደሚካሔድ ተወስኖ የጉባኤው ፍጻሜ ሆኗል።



## ስብከተ ወንጌልን በጋራ እናስፋፋ!

ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌልን በገጠራማና ጠረፋማ ቦታዎች ለማስፋፋት የቤተ ክርስቲያንን የተለያዩ መዋቅሮች የሚያጠናክር የ10 ዓመት ፕሮጀክት ነድፏል። ይህን ታላቅ ተልእኮ ስኬታማ ለማድረግ እርስዎም በሚችሉት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና የበረከቱ ተካፋይ እንዲሆኑ በእግዚአብሔር ስም እንጋብዛለን። የበለጠ ለመረዳት የሰሜን አሜሪካ ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍልን ያግኙን!

eotcmkusa_education@yahoo.com

(240) 899-5215

# ስብከተ ወንጌል

## *ወዴት ነህ? /ዘፍ. ፫፥፱/*

በቀሲስ ብርሃኑ ጎበና

በምክረ ከይሲ ተታልለው ትዕዛዘ እግዚአብሔርን የጣሱት አዳምና ሔዋን ዕራቁታቸውን እንደሆኑ ባወቁ ጊዜ የበለስን ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም በማድረግ የአምላካቸው የእግዚአብሔርን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰምተው በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ። እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ? አለው። /ዘፍ. ፫፥፯-፱/።

የአዳምና የሔዋን ልጆች እንደመሆናችን የውድቀታቸው መንስኤም ሆነ የድኅነታቸው መሠረት ከእኛ ጋር የተገናዘበ ነው። አዳምና ሔዋን ትዕዛዘ እግዚአብሔርን የጣሱት ከጸጋ እግዚአብሔርም ሊራቆቱ የቻሉት እንዴት ነበር? የሚለውን መጠይቅ አንስተን ለውድቀታቸው መንስኤ የሆነውን እንመርምር። በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ የገባው ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን ከእግዚአብሔር መንገድ ያስወጣቸው ደረጃ በደረጃ እያዋዛ መሆኑን እንገነዘባለን። አዳምና ሔዋን ከንጽሕና እርካብ እንዴት እንደወረዱ ስናጤን፡-

- ***መነሻው፡-*** የሔዋንና የእባብ አጉል ጓደኝነት ነው።
  ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ክፉ ባልንጀራ መልካሙን ዓመል ያበላሻል" /፩ ቆሮ. ፲፭፥፴፫/ በማለት እንዳስገነዘበው በእባብ ሥጋ ተሰውሮ የመጣው ሰይጣን ሔዋንን የቀረባት ለማሳት በመሆኑ የሔዋንን ጓደኝነት ለምን ሻተው ብለን አንጠይቅም የመጣበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያዋጣውን መንገድ ሁሉ ከመጠቀም የሚያግደው ነገር የለምና። ሔዋን ግን "ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ ይቀደዳል" እንዲሉ አበው፣ መጀመሪያ ከእባብ ሠላምታ ንግሥተ ሰማይ ወምድር ሳትሆን ንግሥተ ሰማይ ብሎ መጥራቱ ቀጥሎ ክፉ ምክሩ "ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።" ከሚለው የተነሳ ልብዋ ሊጠረጥርና ከእርሱ ጋር ያላትን ግንኙነት ልትቆርጥ ይገባት ነበር። የሌላትን ክብር እንዳላት አድርጋ ሠላምታውን በደስታ ተቀብላ በእባብ ውስጥ ላደረው ባላጋራ ጥርጊያ መንገዱን ማስተካከል አልነበረባትም።

  "ከማያምን ጋር በማያመች አካሄድ አትጠመድ" /፪ ቆሮ. ፮፥፲፬/ እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ አብረናቸው የምንውላቸው ሰዎችና የምንውልበት ቦታ ነው ለመንፈሳዊ ሕይወታችን መዳከምና ብሎም መጥፋት በር የሚከፍተው "ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝና ማንነትህን እነግርሃለሁ" የሚለው አባባል ይህን እውነታ የሚገልጽ ነው። አምኖን በእህቱ ላይ አስነዋሪ ድርጊት ሊፈጽም የቻለው በዚህ የተነሳ በወንድሙ በአቤሴሎም እጅ የተገደለው በኢዮናዳብ ክፉ ምክር መሆኑን ልብ ይሏል። /መጽ. ሳሙ. ካልእ ፲፫፥፭/።

  ስለዚህ መንፈሳውያን ከማን ጋር ልንውል ከማን ጋር ልንመክር ማንን ስለ ሕይታችን ልናማክር እንደሚገባን ማወቅ ይኖርብናል። "ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?" /ማቴ. ፯፤፲፮/ እንዳለ ጌታ በሕይወት ከማይመስሉን ሰዎች ለመንፈሳዊ ሕወታችን የሚጠቅም አንዳች ነገር እናገኛለን ብለን አንጠብቅ።

- **ምኞት፡-** በእባብ ሥጋ የተሰወረ ዲያብሎስ ሔዋንን ጓደኛ ካደረገ በኋላ የመጀመሪያ ተግባሩ ያደረገው በሔዋን ልቡና ውስጥ ምኞትን ማስረጽ ነበር። "በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዟልን?" የሚለውን ተንኮል ያለበትን ጥያቄ የጠየቀው ክፉ ምኞትን በሔዋን ሕሊና ላይ ለመትከል መንገድ ሲከፍት ነው እንጂ ይህ ተሰውሮት አልነበረም። የተደገሰላትን መጥፎ ድግስ ያላወቀች ሔዋን ገር ገሩን በማሰብ "በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ እግዚአብሔር አለ፡- እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።" በማለት መለሰች።

  ያሲያዘችውን ጫፍ ይዞ ወደ እርሱ ፈቃድ በምኞት ይስባት ጀመር "ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉውን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ" የእብድ ባልንጀራ ድንጋይ ያቀብላል እንዲሉ ክፉው ባልንጀራ ዲያብሎስ ለሔዋን በእግዚአብሔር ላይ የምትወረውረውን የክህደት ድንጋይ በእጅዋ አቀበላት። "ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች" የሚለውን አባባል ስንመረምረው እናታችን ሔዋን ከዚያ በፊት አስጎምጅቷት የማያውቀው የበለስ ፍሬ ዛሬ እንዴት ሊያስጎመጃት ቻለ? አዳምና ሔዋን በገነት የኖሩት ሰባት ዓመት እንደሆነ ሊቃውንት ያስተምራሉ ይህን ያህል ዘመን በገነት ስትኖር ትዕዛዘ እግዚአብሔርን መሠረት አድርጋ አይደለም ለመብላት ለማየት እንኳን ያልደፈረችውን ለመብላት እስከ መጎምጀት ያደረሳት ምንድር ነው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው፤ ዲያብሎስ በልብዋ ላይ የተከለው አምላክ የመሆን ምኞት ነው።

  በሕገ እግዚአብሔር አጥር ታጥረን ከምንኖርበት መንፈሳዊ ሕይወት በሰይጣን ተገፍተው በቀረቡንም ሆነ እኛው ይሆኑናል ብለን ባቀረብናቸው የክፋት ኃይሎች አማካይነት ያልኖርንበት ወይንም አሽቀንጥረን የመጣነው የዓለም ሕይወት አስደሳችነት ይተረክልናል። ክፉውን ዘር በሕሊናችን እንዲዘሩ በጎ ፈቃዳችንን ያገኙት ወገኖች በምኞት ፈረስ አፈናጠው ሽምጥ አስጋልበው ሲመልሱን በዓለም ምኞት እንጠለፋለን "እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል" /ያዕ. ፩፥፲፬/ እንደተባለው ተዳፍኖ የነበረውን ፈቃደ ሥጋችንን እንዲያነሳሱት እርነት በሰጠናቸው ሰዎች አማካይነት በምኞት ማዕበል እንዋጣለን።

- **ድፍረት፡-** ዲያብሎስ በሕሊናዋ አምላክ የመሆን ምኞትን ከለኮሰባት በኋላ እናታችን ሔዋን የድፍረት ኃጢአት ገዛት። ለሰባት ዓመታት ያህል በፍጹም ታዛዥነት ጠብቃው የኖረችውን ሕግ ዲያብሎስ በምኞት ፈረስ ሽምጥ ባስጋለባት በዚያች ቅጽበት ናደችው። ለመብላት ያማረ፣ ለዓይን የሚያስጎመጅ፣ ለጥበብም መልካም እንደሆነ የታያትን ፍሬ ወሰደችና በላች ለባልዋም አበላች። የፈጣሪዋን ትዕዛዝ ለመተላለፍ ምክረ ዲያብሎስ ድፍረት ሰጣት።

  በእኛም ላይ ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ የሚያርገው ይህንኑ ነው። በምኞት ሰመመን ይወስደንና ሕገ እግዚአብሔርን በድፍረት እንድንጥስ ያደርገናል በፍጹም

ትህትና የተመላለስንበትን ሕይወት በቅጽበት ለውጠን በትዕቢት እንታጀራለን፣ በአፍአ ሳለን እናከብራት የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ውስጥዋ ስንገባ የደፋሮችን ምክርና አካሄድ ተከትለን እንደፍራታለን፣ ለዘመናት የኖርንበት መንፈሳዊውን ሕይወት በአጓጉል ሰዎች አደፋፋሪነት ምን ይመጣብኛል በሚል ድፍረት እንተወዋለን።

በድፍረት የጣሱት ትዕዛዘ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከፀጋ እግዚአብሔር አራቆታቸው እንጂ የተመኙትን አምላክነት አላስገኘላቸውም።

- ***የፀጋ መገፈፍ፦*** በምክረ ከይሲ ተመርተው ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ጥሰው የበሉት በለስ ለአዳምና ሔዋን አይደለም የአምላክነት ክብር ሊያስገኝላቸው እንዲህ ተብሎ እንደተገለጸው የሰውነት ክብርንም አሳጥቷቸዋል "የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ" /ዘፍ. ፫፥፯/።

  በድፍረት የጣሱት ሕገ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከእግዚአብሔር ለይቷቸዋል። ከእግዚአብሔር መለየታቸው ደግሞ በፀጋ ከእግዚአብሔር አግኝተውት የነበረውን ሁሉ እንዲያጡ አድርጓቸዋል። ዕራቁታቸውን መቅረታቸው የሚያሳየው ይህንን ነው። አዳም በተፈጠረ በአርባ ቀኑ ሔዋን በተፈጠረች በሰማንያ ቀኗ ያገኙትን የልጅነት ፀጋ አጥተዋል። የሚከተለው መርገም ደርሶባቸዋል "በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛዋለሁ በጭንቅ ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል እርሱም ገዥሽ ይሆናል። አዳምንም አለው፦ የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ። ወደ ወጣህባት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና።" /ዘፍ. ፫፥፲፮-፲፱/።

  ዛሬም ቢሆን የተሻለ ሕይወት የሚገኝ መስሎን ሕገ እግዚአብሔርን በድፍረት ጥሰን በመሄድ የምናገኘው ምንድር ነው? ሰላም የሌለበት፣ በሥጋት የታጠረ፣ ጭንቀት የሞላበት ሕይወት ፀጋ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በሚሆንበት ጊዜ የምንለብሰው ያሞቀናል ያደምቀናል፤ የምንበላው ያጠግበናል ጤና ይሆነናል፤ የምንጠጣው ያረካናል፤ የምንሠራው ይባረክልናል፤ ጥቂቱ ይበዛል ከሥጋት ነጻ የሆነ ሰላማዊ ኑሮ እንኖራለን። ወዴት ነህ? የሚለው ጥያቄ የለብንም በተሰማራንበት ጸንተናልና ሕገ እግዚአብሔርን በድፍረት በመጣሳችን ራሳችንን የምንሸሽግበት መሸሸጊያ ፍለጋ አንማስንም። ከወንጀል፣ ከሕሊና ወቀሳ ከሰሳ ነፃ ነንና ማድረግ የሚገባንን በማን አለብኝነት ሳናደረግ ቀርተን ከሚመጣብን ፍርድ እንድናለን።

  በድፍረት ሕገ እግዚአብሔርን የሚጥሱ ሰዎች ፀጋቸውን ስለሚገፈፉ እንደ አዳምና ሔዋን ዕርቃናቸውን መሆናቸው ስለሚታወቃቸው ሁልጊዜ ከለላ የሚሆናቸው ጥሻ ያስሳሉ ግን ነውራቸውን ለመሸሽግ የሚያደርጉት ሩጫ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው። ሰው በክፉ ስራው ከሰው ቢሸሽግ ከሕሊናው ግን መሰወር አይችልም። ስለምንጥሰው ሕግ የሕሊና ወቃሽ እንዳለብን ማስተዋል ይገባል። ስለዚህ የዚህ ሁሉ መፍትሄ፣ የተገፈፍነውን ፀጋ ለማስመለስ ንስሐ የማያወላዳ ምርጫ ነው።

- **የሞት ፍርድ፦** "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ።" /ዘፍ. ፪፥፲፯/ የሚለውን አምላካዊ ቃል አዳምና ሔዋን ተላልፈው በተገኙ ጊዜ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ አግኝቷቸዋል።

  "ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች" /ያዕ. ፩፥፲፭/ እንደተባለ በእባብ ሥጋ የተሰወረ ዲያብሎስ በሔዋን አእምሮ ላይ የሳለው ከንቱ ምኞት በፍጥነት አድጎ ኃጢአትን ወልዷል። በድፍረት ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ጥሰው በለስን ቀጥፈው በልተዋል። በዚያች ቅጽበት ሞተ ነፍስ አግኝቷቸዋል ማለትም ፀጋቸው ተገፍፏል፣ ባሕርያቸው ጎስቁሏል፣ ክብራቸውን አጥተዋል። በኋላም የሥጋ ሞት አግኝቷቸዋል፤ በአካለ ነፍስም ወደ ሲዖል ወርደዋል።

  የዓይናችንን አምሮትና የሥጋችንን ፍላጎት ብቻ ተከትለን የኃጢአት ተገዥ ከሆንንበት ሕይወት በፍጥነት በንስሐ ካልወጣን የእኛም ዕጣ ያው ነው። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ "ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስሐ ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ።" /ራእ. ፪፥፭/።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር


**የሬዲዮ ቤተሰብ አባል ለመሆን ይሻሉ?**

ማኅበረ ቅዱሳን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲሁም በከተማው ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በሚያደርገው ጥረት አዲስ የሬድዮ ፕሮግራም በቅርቡ ይጀምራል። ከሚከተሉት መገናኛ መንገዶች አንዱን በመጠቀም ለዓመት የ100 ዶላር፣ የ50 ዶላር፣ ወይም የ30 ዶላር አስተዋጽኦ ማድረግና የአብርሃም፣ የይስሃቅ፣ ወይም የያዕቆብ የሬድዮ ቤተሰብ አባል መሆን እንደሚችሉ በደስታ እንገልጻለን፦

eotcmkusa_hymn@yahoo.com
(425) 442-5290
(425) 442-3128
(404) 932-4658

# ኪነ ጥበባት

## የጃፓን ትዉስታዬ

በደረጀ ተድላ

የጃፓንን አየር መተንፈስ ከጀመርኩ ስድስት ወራት አልፈውኛል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ በርካታ ነገሮችን ታዝቤያለሁ፣ አድንቄያለሁም። በቴክኖሎጂ ዕድገት ጣራ የነካችው የቶኪዮ ከተማ በሥጋዊ ሩጫ ብቻ ሽምጥ ለጋለበባት ምናልባትም ያለብዙ ድካም ለወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚነት ታበቃው ይሆናል። በመንፈሳዊ መነጽር እየተመራ ሩጫውን ለሚያከናውን ሰው ግን የተሰሎንቄ አምሳያ የሆነችው ብልጭልጯ ቶኪዮ በቀላሉ አትንበረከክለትም።

በእርግጥ የጃፓናውያንን የሥልጣኔ ጥበብ ማድነቅ ተገቢ ቢሆንም "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው" የሚለውን እውነት በዜሮ በማባዛታቸው ሥልጣኔያቸውን ትርጉም አሳጥቶብኛል። በተለይ ደግሞ እኔም ሆንኩ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚኖርባት የቶኪዮ ከተማ እግዚአብሔርን ለማስተናገድ ቦታ አጥታለች። በከተማዋ ወደ 13 ሚሊዮን ጃፓናውያን ይኖራሉ። ወደ 500 ሺ የሚደርሱ የውጭ አገር ዜጎች ይኖራሉ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ወደ 250 የሚጠጉት ኢትዮጵያውያን ናቸው።

የአገሪቱ ዋነኛ ሃይማኖት ቡድሒዝም ነው። ሃይማኖት የለሹም የዚያን ያህል ይሆናል። በከተማዋ ኃጢአት ይቦካል፣ ኃጢአት ይጋገራል። የእግዚአብሔር ዉለታ አይታሰብም። እንደውም አብዛኛዎቹ "ለእራሴ እኔ አምላክ ነኝ" ሲሉ ይደመጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ ለውጭ አገር ሰዎች ያላቸውን ጥላቻ ቃላት አይገልጹትም። በአጠቃላይ የሚታዩት ሆነም የሚዳሰሱት ነገሮች ሁሉ ሥጋ የሚያስደስቱ አንጂ ለነፍስ ጌጥ መሆን አልቻሉም።



በአገር ቤት እያሉ የዕጣኑ መዓዛ እያወዳቸው፣ በጸበሉ እየተፈወሱ፣ በአባቶች መስቀል እየተባረኩ፣ ለኖሩ ምዕመናን ክርስትና በማይታወቅበት በዚህች አገር መኖሩ በራሱ እጅግ ፈታኝ መሆኑን በርካታ ኢትዮጵያውያን አጫውተዉኛል። ትዝ ይለኛል ገና 'ለሰዉ እንግዳ ለአገሩ ባዳ' በሆንኩበት በመጀመሪያዎቹ ወራት ዉስጥ ነው። መጀመሪያ የተዋወቅኳቸው አንድ ወንድምና አንዲት እህት ቤተ ክርስቲያን ሊወስዱኝ በገቡልኝ ቃል መሠረት ይዘውኝ ሄዱ። ኦቻና ሚዙ የሚባል ስቴሽን ደረስን። ሃምሳ ሜትር ያህል እንደተራመድን ከፊት ለፊታችን አንድ ትልቅ ካቴድራል ይታየኛል። በጣም ገረመኝ "ጃፓን ላይ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን?" ለራሴ ያቀረብኩት ጥያቄ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንዘልቅ ግራ ገባኝ። የማየው ነገር ሁሉ ቀድሞ ከማውቀው የተለየ ነው። ሩሲያውያን መሆናቸው ተነገረኝ። ቤተ ክርስቲያኑም የሩሲያውያን እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ።

በእርግጥ አንዳንድ አበሾች "ኦርቶዶክስ" የሚለውን ስያሜ ከማየት ባሻገር በኢትዮጵያና በሩሲያ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን የዶግማ ልዩነት ባለመረዳታቸው አዘውትረው እሁድ እሁድ በቅዳሴ ሥርዓቱ ይሳተፉ ነበር። ልጆቻቸውንም ያስቆርቡ ነበር።

ቀስ በቀስ ግን ወንድሞች ቤት ለቤት ባደረጉት ትምህርት አብዛኛዎቹ አበሾች በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን ልዩነት በመረዳታቸው መሄዳቸውን አቆሙ።እግዚአብሔር ያሳሰባቸው ክርስቲያኖች ዘዴ ዘየዱ። ዘወትር እሁድ ጠዋት ጠዋት እየተሰባሰቡ የራሳቸውን ጸሎት አድርገው፣ ትምህርት ተምረውና መዝሙር ዘምረው መለያት ተጀመረ። እግዚአብሔርን በማያውቁ ሰዎች መካከል ሆኖ እግዚአብሔርን ማምለክ እንዴት ደስ ይላል!! ፈተናውም ግን የዚያኑ ያህል ነበር። ጥቂት ወንድሞችና እህቶች የመኖሪያ ወረቀትም የላቸውም ነበር። እንደልባቸው መንቀሳቀስ አይችሉም። ሆኖም ጉባዔው እየጠነከረ ሲሔድ ወንድሞችና እህቶች በኅብረት ጸሎት በመጠንከራቸው አብዛኖቹ ክርስቲያኖች ጊዜያዊ መንቀሳቀሻ ፈቃድ አገኙ። የዚያኑ ያህል ጉባዔውም በሁሉም መስክ እያደገ መጣ። ታላላቅ መንፈሳዊ በዓላትን በኅብረት በዝማሬ እና በወንጌል ማክበር ጀመርን። ሁላችንም በተዋረድንበት አገር ያከበረንን የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔርን አመሰገንነው። እግዚአብሔርም ለቃሉ ታማኝ ነውና ጉባዔያችንን ይበልጥ አሰፋልን።

መሻትን የሚመለከት አምላክ አንደቸርነቱ ሆነና ከራሳቸው ከጃፓናውያን የኦርቶዶክስ አባት ሰጠን። አቡነ ቶማስ ካናዛኪ ይባላሉ። ግብጽ አገር ከ25 ዓመታት በላይ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመማር ቅስናና ምንኩስናን ተቀብለው ለወገኖቻቸው ብርሃን ለመሆን ዳግም ወደ ጃፓን የመጡ አባት ናቸው።

የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን በማቋቋማቸውና አገልግሎቱም ከመቼውም ጊዜ በላይ በመጠናከሩ የደስታ ስካር አሰከረን። በባዕድ አገር ያገኘናቸው አባታችን አማርኛ ማውራት ባይችሉም አበሾቹ ጃፓንኛ ስለሚችሉ በመካከላችን ጥሩ መግባባት ነበር። እሳቸውም ሁሌም ከቅዳሴ በኋላ በፕሮግራማችን መሃል በመገኘት አባታዊ ምክር ይለግሱናል። ጸበል ጻዲቅ ስናዘጋጅም ተለይተውን አያውቁም። በአጠቃላይ ከአንድ ካህን የሚጠበቀውን ሁሉ ይፈጽሙልናል። ስለ አቡነ ቶማስ በሌላ ጽሑፍ በደንብ አስነብባችኋለሁ። የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ምስራቃዊቷን አገር በወንጌል ጨውነት ያጣፍጥልን። አሜን!!



# የሐመረ ኖኅ እንግዳ

## ቆይታ ከሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ አለማየሁ ጋር

በአሁኑ ሰዓት በሰሜን አሜሪካ የምዕራብ ስቴቶችና ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት በሥራ አስኪያጅነት እንዲሁም ዴንቨር፣ ኮሎራዶ በሚገኘው ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በአስተዳዳሪነት እያገለገሉ ይገኛሉ። ከግብፅ የቲዮሎጂ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ በከሳቴ ብርሃን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አስተማሪ ሆነው አገልግሎታቸውን የጀመሩ ሲሆን በቀጣዮቹ ዓመታት ወደ አሜሪካ እስከመጡበት ጊዜ ድረስ የተለያዩ አህጉረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ፣ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ፣ የስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊ፣ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምክትል ዲን እንዲሁም የቅዱስ ጳውሎስ ሰዋስወ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን በመሆን ሲሠሩ ቆይተዋል። በአንድ ወቅት ወደ ደቡብ አፍሪካ ተደርጎ በነበረውና ከፍተኛ ውጤት በታየበት የአገልግሎት ጉዞ ልኡካን ከነበሩት አራት አባቶችም አንዱ ነበሩ። ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ አለማየሁ። እኛም ስለአገልግሎታቸው እና የሕይወት ተሞክሯቸው እንዲያካፍሉን የእዚህ ዕትም የሐመረ ኖኅ እንግዳ አድርገናቸዋል። ይህንን ለማሳካት ላደረጉልን ትብብር ሁሉ ልባዊ ምስጋናችንን እያቀረብን ወደ ቃለ ምልልሱ እናሸጋግራችኋለን። መልካም ንባብ።

**ሐመረ ኖኅ፡-** የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የትና እንዴት ጀመሩ? አሜሪካ ከመምጣትዎ በፊት የት የትና በምን የኃላፊነት ድርሻዎች ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል?

**ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-** በእውነቱ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መነሻው ሲታይ ትንሽ ከበድ ያለ ነው። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰው በሚጀምርበት ጊዜ በውሉ አያውቀውም፤ ከሕፃንነት ጀምሮ ነው የሚጀመረው። ከተማሪ ቤት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አለና ሰላም ለኪ ተብሎ ውዳሴ ማርያም መድገም ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ጨኸቱ ሲገባ ከአገልግሎት መለየት የለምና በሕፃንነት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አለ። ነገር ግን እንደ ጥያቄው መንፈስ እኔ አገልግሎቴን የጀመርኩ የግብፅ የቲዮሎጂ ተማሪ ስለነበርኩኝ ከግብፅ እንደ ተመለስኩኝ በ1968 ዓ.ም. ነው መደበኛ ሥራ የጀመርኩት። በ1968 በአስተማሪነት ተቀጥሬ እሠራ ነበር። በአስተማሪነቱ አገልግሎት ታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ባሠሩት በከሳቴ ብርሃን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ነበር ሥራ የጀመርኩት። ከዚያ ጀምሮ ለተወሰኑ ዓመታት ማለትም እስከ 1972 አካባቢ በአስተማሪነቱ ከቆየሁ በኋላ እንደገና በሀገረ ስብከቱ ትምህርት ክፍል ኃላፊነት እንዳገለግል ተመደብኩኝና በዛው ሳገለግል ቆየሁ።

ከ1979 ጀምሮ በሥራ አስኪያጅነት ተመደብኩኝ፤ እስከ 1983 የትግራይ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ስሠራ ቆይቻለሁ። በአዲስ አበባም ያሳለፍኳቸው ጊዜዎች ወደዚህ ተጠቃልለው ማለት ነው በ1982 ዓ.ም. ከመቀሌ ወደ አዲስ አበባ ተፈናቅለን እንደመጣን ከሥራ አስኪያጅነቴ ሥራ ጋር የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ጊዜያዊ ኃላፊ ሆኜ ነበር ስሠራ የቆየሁት። በ1984 እና 1985 ደግሞ የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ነው የሠራሁት። እነዚህ ሁለት ዓመታት ለእኔ ጥሩ የሥራ ዓመታት ነበሩ። የማልረሳቸው፣ የማስታውሳቸው፣ ብዙ ቁም ነገሮችን የሠራሁባቸውና ያገኘሁባቸው ዓመታት ነበሩ። ከዚህ በኋላ አሁንም በ1985 መጨረሻ ወይም በ1986 እና በ1987 የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ሠራሁ።

በ1988 ደግሞ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ተዛወርኩኝ። የመምሪያ ኃላፊ ሆኜ እስከ 1992 ዓ.ም. አገለግያለሁ። በዚሁ ጊዜ በ1993 እና 1994 የችግር ጊዜ ነበር፤ የተወሰነ ፈተና ነበረብኝ። ከሥራ ውጪ ሆኜ ትንሽ ፈተና የተቀበልኩበት፣ አስፈላጊ ያልሆነ ፈተና ማለት ከዓላማዬና ከሥራዬ ውጪ የሆነ ትርጉም ተሰጥቶ ከሥራ ታግጄ የቆየሁበት ነበር። እንደ እግዚአብሔር ቸርነት ወደ ሥራዬ ተመልሼ አገልግሎቴን ጀምሬአለሁ። ወደ ሥራ ስመለስ የተመደብኩት በስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊነት ነበር። ከሰንበት ትምህርት ቤት ማደረጃ ኃላፊነት የስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊ ሆኜ ሥራ እንደጀመርኩኝ አሁንም ወደ ደቡብ አፍሪካ ለአገልግሎት አራት አባቶች ተላክን፤ ልኡካኑም ክቡር መላከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን፣ የተከበሩ አባ ፍቅረማርያም በአሁኑ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ዳንኤል፣ ክቡር መላከ ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን እና እኔ ነበርን። የደቡብ አፍሪካ አገልግሎት የአገሬው ተወላጆች ወይም ጥቁሮቹ ለቤተ ክርስቲያናችን ያቀረቡትን ጥያቄ መሠረት ያደረገ ሆኖ ኦርቶዶክሳዊ መሠረተ እምነትን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንንና፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ማስተማር ነበር። አገልግሎቱ ለስድስት ወር የቆየ ሲሆን ሁለት ከተሞች እየተመላለስን ነበር የምናስተምረው። ወደ 60 ሺ የሚደርሱ ተገልጋዮች ነበሩ። ቅዳሴው በሙሉ ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሞላቸዋል። እነሱ ደግሞ ከእንግሊዝኛ ወደ ራሳቸው ቋንቋ እንዲተረጉሙ ተደርጓል። በደቡብ አፍሪካ ጥሩ አገልግሎት በመስጠቱ መሠረት ያለው ሥራ ተሠራ ማለት ይቻላል። ከደቡብ አፍሪካ ተመልሼ ወደ ስብከተ ወንጌል መምሪያ ገባሁ። አሁንም የአቅሜን ያህል ሳገለግል ቆየሁ። በዚሁ ጊዜ ለስድስት ወር ያህል የቅድስት ሥላሴ ምክትል ዲን ሆኜ እንድሠራ ተደርጎ ነበር። እንደገና ወደ መጨረሻው አካባቢ የቅዱስ ጳውሎስ ሰዋስወ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ አሁንም ዲን ሆኜ እንድሠራ ተመድቤ ነበር። እንደዚህ ሆኜ ሳገለግል ቅዱስ ጳውሎስ ሰዋስወ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ አገልግሎት ላይ እያለሁ ወደ አሜሪካ የመጣሁበት ዘመን ነውና ባጭሩ ተጠቃልሎ ሲታይ የአገልግሎቴ ሁኔታ ይሄንን ይመስላል።

**ሐመረ ኖኅ፡-** ወደ አሜሪካ እንዴትና መቼ መጡ? ምንስ እየሠሩ ይገኛሉ?

**ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-** ወደ አሜሪካ የመጣሁት እኔ ሳላውቀው እግዚአብሔር ፈቅዶ በ1998 ወይም በፈረንጆቹ 2005 ዓ.ም. ነው። አሁን ስድስት ዓመት ሊሆነኝ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አሜሪካ እመጣለሁ ብዬ አስቤም አልሜም አላውቅም። አሜሪካ እመጣለሁ የሚል ሕልም የለኝም ነበር። እግዚአብሔር ፈቅዶ እዚህ ስመጣ ደግሞ እንደመጣሁ ቤተ ክርስቲያን ተዘጋጅቶ ነው የጠበቀኝ። የ[ዴንቨር] መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዲስ ቤተ ክርስቲያን ነበር። ስለዚህ ያ ቤተ ክርስቲያን ገና አባት የለውም ነበርና እኔ እንደምመጣ ሲታወቅ [በጊዜው የሰሜን አሜሪካ ሊቀጳጳስ የነበሩት] ብፁዕ አቡነ ማትያስ ከዚህ ካሉ አባቶች ወይም ወንድሞች ይመስለኛል ተደዋውለው ባገኙት ኢንፎርሜሽን መሠረት ስልክ ደውለው አንድ ቤተ ክርስቲያን አንተን የሚጠብቅ ስለሆነ ለሌላ ቃል እንዳትገባ ያንን ቤተ ክርስቲያን አንተ ነህ በኃላፊነት የምታስተዳድረው ብለው መመሪያ ሰጡኝ። ወዲያው ተነጋግረን እንደመጣሁ በቀጥታ ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነው፤ ቅዳሜ ገብቼ እሁድ ነው ቅዳሴ የጀመርኩት። ከዚያ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ እንዳለ ሆኖ የምወዳቸውና የማከብራቸው ወንድሜ ቀሲስ ደጀኔ በኋላ መላከ ሰላም ደጀኔ አንድ ስድስት ወር ቆይተው መጡልኝ። አብረን ነው አሁን እያገለገልን ያለነው። አሁን የራሳችን ቤተ ክርስቲያን ገዝተን በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጠን ነው ያለነው። አሁን ብቻዬን አይደለም እያገለገልኩ ያለሁት።

ከዚሁ አብሮ ምናልባት እንደ እግዚአብሔር እኔ አሁንም ያላሰብኩት ካለፈው ተሞክሮዬም ትንሽ ያልፈለግኩትም ማለት ይቻላል በሥራ አስኪያጅነቱ እንዳገለግል ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ኃላፊነት ስለጣሉብኝ ከዚያ በኋላ ደግሞ ያ ኃላፊነት ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ አልፎ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትሪያርካችን የግድ ይሄንን ኃላፊነት መወጣት አለብህ ብለው ደብዳቤ ስለሰጡኝ እስካሁን ድረስ በሥራ አስኪያጅነቱም በተደራቢነት በማገልገል ላይ እገኛለሁ እና ያው የአገልግሎቴ ሁኔታ ይሄንን ይመስላል።

*ሐመረ ኖኅ፡-* በሥራ አስኪያጅነት እያገለገሉ ያሉት በሰሜን አሜሪካ የምዕራብ ስቴቶችና ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ነው?



ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ አለማየሁ

*ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-* አዎ እንደሱ ነው። ምዕራቡ ክፍለ አሜሪካ ሀገረ ስብከት እንግዲህ አሁን ባለው መዋቅር በፊት ብፁዕ አቡነ ማትያስ በነበሩ ጊዜ መላው ሰሜን አሜሪካ አንድ ሀገረ ስብከት በአንድ ሊቀ ጳጳስ ነበር የሚመራው። እሳቸው ወደ ኢየሩሳሌም ሲዛወሩ ሀገረ ስብከቱ በሦስት መዋቅር ተከፈለ። እና ከሦስቱ አህጉረ ስብከት አንዱ የምዕራቡ ክፍለ አሜሪካ ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ነው የእኛ፤ እና የዚያ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ነው እየሠራሁ ያለሁት።

*ሐመረ ኖኅ፡-* በሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ የኃላፊነት ዘመንዎ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር የነበረዎ የሥራ ግንኙነት ምን ይመስል ነበር? እንዴትስ ያስታውሱታል?

*ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-* በእውነት የማስታውሰው በመልካም ሁኔታ ነው። ጥሩ ትዝታዎች አሉኝ። ማኅበሩ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች እኔ አቅሜ በፈቀደ መጠን የማኅበሩን እንቅስቃሴ አውቃለሁ ብዬ እገምታለሁ። የማኅበሩን እንቅስቃሴ በማወቄ ደግሞ ከማኅበሩ ጋር ጥሩ ትሥሥር ፈጥሮልኛል። ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረኝ አድርጓል። ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች ሌላ ትርጉም እየሰጡ በእኔ ላይ ያደረጉት ዘመቻ እንዳለ ሆኖ የደረሰብኝ ፈተና እንዳለ ሆኖ የሚያስደስተኝ ግን ይህንን ማኅበር እንደ ቋሚ ሥራ እንደ ቋሚ ሐውልት አድርጌ የምገነዘበውና የምወስደው በየዩኒቨርሲቲው፣ በየኮሌጁ፣ በየተቋማቱ የሚሰጣቸው የጉባኤ ትምህርቶች ወጣቱ ከቤተ ክርስቲያን እንዳይወጣ በማድረግ፣ ወጣቱ በመናፍቃን እንዳይማረክ በመናፍቃን እንዳይነጠቅ፣ ባልሆነ አጉል ልምድና አጉል እምነት ተሳስቶ እንዳይሔድ የሚያደርገው መሠረታዊ ሥራ ነው። ይህ ማኅበር የሚሠራው ሥራ በእውነት ትልቅና ቋሚ ሥራ ነው። ለዚሁ በምንም መልኩ ሌላ ሚዛን ሊሰጅለት የሚገባ አይደለም። በእኔ አስተሳሰብ በእኔ አቅም ከዚህ የበለጠ ለቤተ ክርስቲያን ዋንኛ ሥራ ምንም ነገር የለም። ስለዚህ ማኅበሩን የማከብረው፣ ማኅበሩን የምወድበት ምክንያት፣ ማኅበሩን በልቤ እንዲያድር ካደረጉ ምክንያቶች አንዱና ዋንኛው ይህ አገልግሎት ነው። ይህ ዓይነቱን አገልግሎት በቅርብ ስለምከታተል፣ በቅርብ አውቅ ስለነበር፣ በቅርብ እኔም ራሴ ገብቼበት አገልግሎት የሰጠሁባቸውም ጊዜያት ስላሉ በየሀገረ ስብከቱ መቀሌ፣ ጅማ፣ ሌሎችም ተቋማት ዲላ ድረስ ሔጃለሁ። እና እነዚህን ሁሉ እያየሁ በእጅጉ የሚያረካ ሁኔታ ስላገኘሁ በጣም በጥሩ መንፈስ ነው ትዝታ ያለኝ።

እኔ ለማኅበሩ የምሳሳው ነገር ምንድን ነው ማኅበሩ በትክክለኛው እንደነበረው፣ እንደማውቀው፣ እኔ እንደምገነዘበው ማለት ነው በዚያው ሕይወት እንዲቀጥል አሁንም እመኛለሁ። ስለዚህ ከማኅበሩ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ግልጽና የጠበቀ ግንኙነት ነበር። የእኔ አቋም ግልጽ ነው፤ የማኅበሩም በእኔ ላይ ያለው ግንዛቤ እንደዚሁ ይመስለኛል። አዲስ አበባን ለቅቄ እስከመጣ ድረስ በማኅበሩ የነበረኝ ወይም ያለኝ እምነት ይህንን ይመስላል። እኔ በዚህ ማኅበር ምክንያት ብዙ ፈተና ደርሶብኛል ብዬ የምለው ነገር ባይኖርም መጠነኛ ችግሮች ግን አሳልፌአለሁ። መጠነኛ ችግሮችን ሳሳልፍ ግን ለማኅበሩ ከመቆርቆር፣ ለማኅበሩ ከማሰብ አይደለም። ማኅበሩን ከዚህ አድነዋለሁ ብዬ እኔ አስቤ አይደለም። ከቤተ ክርስቲያኔ ዓላማና አገልግሎት አንጻር ብቻ ነው የማኅበሩን አገልግሎት እንድወድ ያደረገኝ እንድደግፍም ያደረገኝ። አሉባልታዎች ይኖራሉ። አሉባልታዎች ከባለሥልጣን ጋር ለማጣላት የማይሸረቡ ሁኔታዎች አልነበሩም። ተብሎ ተብሎ ሲያቅት "ኃይለ ሥላሴ ይህንን ማኅበር ደጋፊ ሆኖ እንዲሁ ጠበቃ ሆኖ የቆመው አለምክንያት አይደለም። ማኅበሩ ቋሚ ደሞዝ ስለመደበለት ነው" እስከመባል ተደረሰ። እንደውም ደሞዙ እንዲሁ በቀላል የሚገመት አይደለም "3000 ብር ወርሃዊ ደሞዝ ተመድቦለት ነው" ተብሎ ነው ለቅዱስ ፓትሪያርኩ የተነገረቸው። እኔ በእውነቱ 3000 የሚመድብልኝ ማኅበር ቢኖር ኖሮ ዓዜን ጠቅልዬ ከቤተ ክህነት ወጥቼ የማኅበሩ ደንበኛ ቋሚ ሠራተኛ መሆን እችል ነበር። ነገር ግን እኔ በደሞዝ ይህንን ማኅበር አላውቀውም። መጻሕፍት በምጽፍበት ጊዜ ለምጽፍበት አገልግሎት የወረቀት መግዣ የእስክሪብቶ መግዣ ተብሎ ለተወሰኑ ጊዜያት የሚሰጥ የሥራ ማስኬጃ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ጸሐፊዎች የሚሰጥ ክፍያ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ክፍያ አላውቅም። ከዚህ ማኅበር ደሞዝም አልጠብቅም። እና የሚከፈለኝ ደሞዝ የለም ሰውች ግን እንደዚህ ነው ስለው ያቀረቡኝ። እኔ ግን ያልሆንኩትን ሆነሃል ቢሉኝ ብዙም አይደንቀኝም። የሆነው ሆኖ ጠቅለል ባለ መልኩ ግንኙነቱ ጥሩ ነበር፤ ትዝታው አሁንም ጥሩ ነው።

*ሐመረ ኖኅ፡-* የማኅበረ ቅዱሳን አባላት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማለትም በቤተ መቅደስ፣ በስብከተ ወንጌል፣ በገዳማትና አድባራት መርጃ አጽራረ ቤተ ክርስቲያን በመከላከል እና በሌሎችም የሚሰጡትን አገልግሎት እንዴት ይገመግሙታል?

*ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-* ከዋናው ማዕከል የማውቀውን መናገር እችላለሁ። አሁን እዚህ ሰሜን አሜሪካ ያለው አገልግሎት ይህንን ይመስላል ብዬ ምስክርነት መስጠት አልችልም። ወደ አሜሪካ ከመጣሁ ጀምሮ ከማኅበሩ ጋር ያለኝ አገልግሎት በጣም የተዳከመ ስለሆነ ይህንን ይመስላል፣ ይህ ይጐድልበታል፣ ይህንን አሟልቷል ብዬ የምሰጠው ብዙ [አስተያየት] አይኖርም። በጥንት በመሠረቱ እንደማውቀው ግን ገዳማትና አድባራትን መርዳት አንዱ ተግባሩ እንደሆነ አውቃለሁ። ስብከተ ወንጌልን ማጠናከር ተቀዳሚ ዓላማው ነው። በቤተ መቅደስ አገልግሎት ምናልባት አሁን አሁን ብዙ ወጣቶች የስብከተ ወንጌል ማጠናከር ተግባራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ቤተ መቅደስ ብቅ ብቅ እያሉ ይመስለኛል። ብዙ ወጣቶች ካህናት እየተፈጠሩ ነው። ጥሩ ነው፣ ይሄ ነገር ጥሩ ነው። ነገር ግን በዚሁ ላይ ሊጨመርበት ሊተኮርበት የሚገባ አንድ ነገር አለ። የቤተ መቅደስ አገልግሎት ሲጀመር የቤተ መቅደሱ አገልግሎት የሚከናወንበት የቅዳሴው ሁኔታ፣ የዜማው ሁኔታ ደግሞ ሊተጉበት ይገባል። እና ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው አጠናክረው የክህነቱንም አገልግሎት ልዩ ትኩረት ሰጥተው ሊያጠኑት ይገባል የሚል እምነት አለኝ እንጂ በመሠረተ አላማው

ጥሩ ነው። ግብፆች ከእኛ የሚሻል አገልግሎት መስጠት የቻሉት ዘመናዊያን ካህናት ስላሏቸው ነው። የትውልዱን ቋንቋ የሚያውቁ ካህናት ስላሏቸው ነው። ትውልዱን በሚያውቀው ቋንቋ በሚያውቀው ደረጃ ስለሚያገለግሉት ነው። የግብፅ ካህናት ሕዝቡ የሚያውቀውን ያውቃሉ። ሕዝቡ የሚጠይቃቸው ሁሉ እንግዳ የሚሆንባቸው አይደሉም፤ መልስ የሚሰጡ ናቸው። መንፈሳዊው ዕውቀት ደግሞ የግላቸው ነው። ከምዕመናን የሚበልጡበት የሚለዩበት ምክንያት አላቸው፤ ይኸውም የመንፈሳዊ ዕውቀታቸው ነው። ምክንያቱ የግብፅ ካህን ቢያንስ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪውን ተቀብሎ ወደ ቲዮሎጂ ይገባል እንጂ ምንም ነገር ሳይይዝ ቲዮሎጂ የሚማር ካህን አይኖርም። የእኛ ችግር ምንድን ነው ከሥር መሠረታችን የምንጀምረው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ብቻ ነው። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ዕውቀት አባቶቻችን ሙሉ ሆነው እያለ በዘመኑ ዕውቀት ግን ሕዝቡ እየቀደማቸው እየሄደ ወይም እየቀደመን እየሄደ ትንሽ ሳንቸገር አልቀረንም። ታዲያ ለዚህ ችግር ልጆቻችን ወንድሞቻችን በዚሁ በዘመኑ የበሰሉ ባለሙያዎች በመሆናቸው ያንን የክህነት አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት ጊዜ ጥሩ የበለጠ አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚችሉ ተስፋ እናደርጋለን። እንደዚህ በሚባልበት ጊዜ አሁን ያልኩት ነገር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ለማለት ነው። የቤተ መቅደስ አገልግሎት የተሟላ ሲሆን ነው ጥሩ ውጤት ሊገኝበት የሚችለው እና የቅዳሴው ነገር፣ የዜማው ነገርም ልክ እንደ ስብከተ ወንጌሉ ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባቸዋል። ጊዜያቸውን አጥፍተው ይሄንን ሊተጉበት ይገባል።

አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ለመከላከል ስለሚደረገው ጥረት እውነቱን ለመናገር ከሆነ አሁንም የዋናውን ማዕከል ነው እየተናገርኩ ያለሁ። በዚህ በሰሜን አሜሪካ ያለው አሁንም እንደዚሁ እየቀጠለ ነው አልቀጠለም እኔ ብዙ አላውቅም። ነገር ግን የማኅበሩ ትልቁ ተግባር ይሄንኑ ነው። መናፍቃን ራሳቸው ምስክርነታቸውን ሳያፍሩ ሳይቸሩ የሰጡበት ምስክር ነው። ያው "በዚህች ቤተ ክርስቲያን መንቀሳቀስ ያልቻልነው ማኅበረ ቅዱሳን የሚባል ጠላት የምሁራን ድርጅት ስላለ መንቀሳቀስ አልቻልንም" እስከሚሉ ድረስ ነው ማኅበሩ እያገለገለ ያለው። ይህ ነው የሚፈለገው። ይህ ነው ሁላችንንም ተስፋ እንድናደርግ የሚጋብዘን። ስለዚህ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ለመከላከል የሚደረገው የማኅበሩ እንቅስቃሴ አሁንም መቀጠል አለበት። በዚሁ ካልቀጠለ መናፍቃን ዕቅዳቸው ረዥም ነው። ዕቅዳቸው አሁንም ይህችን ቤተ ክርስቲያን ለማሰናከል ነው። የራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ምን ላይ እንዳለ መሠረታቸው በመናድ ላይ እንዳለ እያወቁ ተያይዞ ለመጥፋት ትውልዱን በሚሰማው በሚመስለው በሚመቸው ሥጋዊ ፍላጐት ሊማርኩት ብዙ ጥረት እያደረጉ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በእውነት የእኛ ልጆች ኢትዮጵያውያን ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ብዙ ሊማሩ ይገባቸዋል። ዛሬ የፕሮቴስታንቱ ዓለም በሚዘጋበት ጊዜ፣ በወደቀበት ጊዜ፣ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩ ወደ መስጊድ እየተለወጡ ባለ ጊዜ ወደ ሲኒማ ቤት እየተለወጡ ባለ ጊዜ ፕሮቴስታንት ሆኜ እዘልቃለሁ ብሎ ማለት በእውነቱ ሞኝነት ነው። ትውልዱ የለም። ሃያና አስራ አምስት ሽማግሌዎች ይዘው የሚንቀሳቀሱት ቤተ ክርስቲያን አሁን በመሸጥ ላይ ነው ያሉ። ይሄ ዝም ብሎ እኛ ስላልነው የሆነ ነገር አይደለም፤ እውነታው ይኸው ነው። ሁላችንም ቤተ ክርስቲያን የገዛነው ከፕሮቴስታንቶቹ ዓለም ነው። ፕሮቴስታንቶች ይገለገሉበት የነበረ ነው። ስላቃታቸው ነው፣ ትውልዱ ስለከዳቸው፣ ትውልዱን ስላጡ አሁን የሚገለገሉበትን ሁሉ በመሸጥ ላይ ናቸው። ስለዚህ የፕሮቴስታንቱ ዓለም ቀጣይ አለመሆኑን እያወቁ እንደገና ተያይዞ ለመጥፋት የጥፋት መረባቸውን በሚዘረጉ መናፍቃን ላይ ጠንክሮ መዝመቱ እኔ ምንም ምንም አይነት ምክንያት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ስላይደለ ሕዝቡ መጠናከር አለባቸው። ያልተሟላ ነገር ካለ እንዲሟላ ማድረግ ነው። ለሰው ተብሎ ሰውን ለማስደሰት ወይም ሰውን ለማሳዘን ከሆነ የሚሰጠው አገልግሎቱ አሁንም እግዚአብሔር የሚጨመርበት አይሆንምና ፈራሽ ነው። ነገር ግን ዋናው ነገር ቤተ ክርስቲያንን ከጥፋት ለማዳን እስከሆነ ድረስ የትኛውም ኃይል የሚከለክለው የሚገታው ሊሆን አይችልም። ይሄን ማመን ማወቅ አለብን። የእግዚአብሔር የሆነን ነገር በእግዚአብሔር ፈቃድ የተደገፈን ነገር በምንም የሚገታው የሚመልሰው ማንም የለም። ይሄ ማኅበር በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመሠረቷል ብዬ አምናለሁ። የሚሰጠውም አገልግሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚታይበት ስለሆነ ያው ውጤት እየታየበት ያለው። ስለሆነም አገልግሎቱ ጠንካራ ነው፣ አገልግሎቱ መልካም ነው፣ አገልግሎቱ በበለጠ ሊጠነከር ይገባዋል። የቀደሙትን ሰዎች ሊያዩ ይገባቸዋል።

የአሁኑ ልጆቻችን የቀደሙ ሰዎች ምን ፈተና አሳልፈው ነው ማኅበሩን ለዚህ ያደረሱት፣ ድንበር ተሻግሮ አሜሪካ እንዲታይ፣ ድንበር ተሻግሮ አውሮፓ በአጠቃላይ በዓለም ላይ መሠረቱን እንዲጥል የሆነው በእነማን ብርታት ነው? እነማን ነበሩ? ምን ችግር ምን ፈተና አሳለፉ? እንዴት ሆነው ነው ማኅበሩን ለዚህ ያደረሱት የሚለውን ነገር ከኋላ እየሔዱ እየተማሩ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ያስፈልጋቸዋል ይመስለኛል ። ከዚህ ውጪ በአጠቃላይ ሲታይ ግሩም የሆነ አገልግሎት ነው። እርግጥ ነው እንደዚህ ብለን ስንል ማኅበረ ቅዱሳን ፍጹም ነው ብለን እንዳይደለ ደግሞ ሁሉም ሊያውቀው ይገባል። ከሰው ፍጹምነት የለም። ፍጹምነት ያለው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። ፍጹምነት የሚኖረው ከእመቤታችን፣ ከመላእክት፣ ከቅዱሳን ብቻ ነው። እኛ ግን ደካሞች ስለሆንን ፍጹምነቱ ላይኖረን ይችላል። ማኅበሩ አገልግሎት በሚጀምርበት ጊዜ እኛ የመሰናክል መረብ እንዘረጋለን። የማኅበሩ አባላት ደግሞ እንደ ልጅነታቸው እንደ ሰውነታቸው በሚደርስባቸው ፈተናም ይሁን ባልታሰበ ባልተገመተ ነገር የራሳቸው ደካማነት ሊያሳዩ ይችላሉ። ይሄ አዲስ ነገር ሊሆን አይችልም ለምን ደከሙም አይባልም። ግን ፍጹማን ናቸው ደግሞ ማለት አይቻልም። ስለዚህ ድክመታቸው ካለ ወደኋላ እያዩ እያስተካከሉ እያረሙ አገልግሎታቸውን ሊቀጥሉ ያስፈልጋል ይመስለኛል። የእኔ ግምት የእኔ ግምገማ ይሄ ነው።

***ሐመረ ኖኅ፡-*** ማኅበረ ቅዱሳን የተመሠረተበትን ዓላማ አሳክቶ ካስቀመጣቸው ግቦች ለመድረስ በቀጣይ ምን መሥራት አለበት? ከአባቶችስ ምን ይጠበቃል ይላሉ?

***ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-*** እንግዲህ ማኅበረ ቅዱሳን የሚጠበቅበት ዓላማውን ያወቀ ዓላማውን ለማሳካት ዓላማውን አክብሮ የሩቁንና የቅርቡን ግብ አውቆ የሚንቀሳቀስ እስከሆነ ድረስ አሁን እንዳልኩት ፈቃደ እግዚአብሔር ሲጨመርበት ሁሉም ነገር የተስተካከለ ይሆናል። እስካሁን ድረስ እየታየ ያለው በዚሁ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ጥሩ ውጤት የሚታይበት ስለሆነ ግቡ ላይ ለመድረስ በቀጣይነት መቀጠል ነው። የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ተለዋዋጭ ዓላማ አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ዓላማ አንድ ዓላማ ነው። የቤተ ክርስቲያን ዓላማ በዓለት ላይ የተመሠረተ አንድ ዓላማ ስለሆነ ያንን ጽኑ ዓላማ ይዞ መንቀሳቀስ ነው አንድን ዓላማ ግብ ሊያደርሰው የሚችለው። እና ያንን የተባልነውን ነገር እያስታወስን "አልቦ ዘይእኅዝ ዕርፈ ወየሐርስ ድኅሪተ /እርፍን ይዞ ወደኋላ የሚያርስ የለም/" /ሉቃ. ፱፥፷፪/ እንደተባለ ይሄንን የተያዘውን ነገር በትክክል ግቡ ላይ ለማድረስ በጽኑ እምነት መሥራት ነው። ምናልባት ግቡ ላይ ለማድረስ በሚባልበት ጊዜ ሰው ሰውኛ ቋንቋ ሊመስል ይችላል። ግቡ ለማድረስ ሲባል አንድ

አላቂ ነገር እዚያው ሔደውበት ፍጻሜ የሚያገኝ ነገር ሲሆን ነው ግቡ መድረስ የሚባለው። የቤተ ክርስቲያን ግብ ግን እስከ መጨረሻ ድረስ ነው እስከ ምጽአት ድረስ አገልግሎት ተፈጽሟል አብቅቷልና ይበቃል የሚባል ነገር አይደለም። ዋናው ነገሩ ያው ስብከተ ወንጌል የእግዚአብሔር ቃል በሕዝብ ልብ እንዲያድር በምድር ላይ ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ቤተ ክርስቲያን እንድትሰፋ ያንን በዓለት ላይ የተመሠረተውን ዓላማ አጥብቆ አጠንክሮ እንዲቀጥሉ ማድረግ ነው ግቡ ላይ መድረስ። ዋናው ነገሩ እምነት ያስፈልጋል። ጽኑ እምነት ካለ ሁሉም ነገር ይሆናል፣ ይከናወናል። የራስን ዓላማ ማወቅ መገንዘብ፣ የራስን ሕይወት መገንዘብ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕይወት መገንዘብ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። ሁላችንም ይሄንን ካወቅን ግባችን ላይ እንደርሳለን። የምናስበውን ነገር ሁሉ ልናሳካ እንችላለን።

ከአባቶች ምን ይጠበቃል መባሉ ምናልባት የተለመደ ቋንቋ ይመስለኛል ከአባቶች ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያን ምን ይጠበቃል ቢባል እኔ የቀና ይመስለኛል። ቤተ ክርስቲያኒቱን ማየት ያለብን በአጠቃላይ ጥቅል ሕይወቷን ነው። አባቶች የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ናቸው፤ በአባቶች ግን በተናጠል የሚታይ ነገር የሚጠበቅ ነገር አይኖርም። ከቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ይጠበቃል? ልጆቿን መሰብሰብ ይጠበቅባታል፣ ልጆቿን ማበረታታት ይጠበቅባታል፣ ለልጆቿ አለኝታ መሆን ይጠበቅባታል። ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የልጆቿ ጠባቂ የመሆኗ የአደራ ምሥጢር በግልጽ የተጻፈ ስለሆነ በተሰጣት አደራ መሠረት ልጆቿን መጠበቅ ግዴታዋ፣ መብቷ፣ ኃላፊነቷ ነው። ይሄ ከሆነ ያው ወጣቶች ደግሞ ቤተ ክርስቲያን አይዟችሁ ብላ ከጐናቸው ቆማ መንገድ ስታሳያቸው መንገድ ስትመራቸው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። እዚህ ላይ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው የሚመስለኝ ምንድን ነው ምናልባት ከእኔ የሚጠበቅ ነገር ባለመፈጸሜ ማኩረፍ የሚቻል አይመስለኝም። እግዚአብሔር ከፈቀደልኝ ከእኔ የሚጠበቀውን ነገር ለልጆቼ አስተላልፋለሁ በአባትነቴ ማለት ነው። እግዚአብሔር ካልፈቀደ ደግሞ ምናልባት እስከሚፈቅድ ድረስ የተወሰኑ ውጣ ውረዶች ይኖራሉ፤ የተወሰኑ እንቅፋቶች ይኖራሉ። ያንን እንቅፋት ለምን ተፈጠረ? ኃይለ ሥላሴ ለምን ይህንን እንቅፋት ፈጠረብን ብሎ በማኩረፍ ወደ ኋላ የሚሸሽ ካለ ገና ዓላማውን ያልተገነዘበ ሊሆን ይችላል። ዓላማን ከተገነዘቡ የክርስትና ሕይወት ከማኩረፍ ውጪ ነው። የክርስትና ሕይወት ከበቀል ውጪ ነው። የክርስትና ሕይወት ያው መልካም በተገኘ ቁጥር ብቻ የሚወደድ ፈተና ሲመጣ ደግሞ የሚሸሹት አይደለም። ክፉውም በጎውም ከእግዚአብሔር የሚመጣ ነገር ነው። ክፉውም በጎውም ለበጎ ነው፣ ለመልካም ነገር ነው እግዚአብሔር የሚያመጣው። ለዚህ ዋናው ነገሩ ዓላማን አውቆ ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቀውን ነገር ቢያገኙም ባያገኙም ዓላማን አጥብቆ መሥራት ነው የሚጠበቅ ብዬ ነው የማምነው።

እንግዲህ ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቀው ምን እንደሆነ ስናስብ ከልጆቻችን የሚጠበቅ ደግሞ ምን መሆን አለበት የሚለው መዘንጋት የለበትም። ሁለቱም ተያያዥ ሆነው የሚቀጥሉ ናቸው። ልጆቻችን የቤተ ክርስቲያናቸውን መዋቅር ጠብቀው፣ ሥነ ሥርዓትን አክብረው፣ በቤተ ክርስቲያን መመሪያ እና በቤተ ክርስቲያን ሕግና ትእዛዝ መሠረት መመራት ግዴታቸው እንደሆነ መብታቸውም እንደሆነ ማወቁ ተቀዳሚ ተግባራቸው መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። አባቶች ደግሞ ለዚህ የሚወጡ የሚደክሙ ልጆችን አይዟችሁ ብሎ ዓላማቸውን አክብረው በዓላማቸው ጸንተው እንዲሠሩ የሚፈለገውን ድጋፍ መስጠት ደግሞ ከአባቶች የሚጠበቅ መንፈሳዊ ግዴታ ነው እላለሁ። ስለዚህ ሁሉም ተያያዥነት ያለው አባቶች ለልጆቻቸው ልጆች ከአባቶቻቸው ሥር ሆነው ማድረግ የሚገባቸውን ነገር እንዲያደርጉ ተጠባብቆ የመሥራት ሁኔታ እንዳለ ይሰማኛልና በዚሁ ቢሆን አገልግሎቱ ቀና ይሆናል። የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት የሰመረ ይሆናል።

እንግዲህ እኔ ማኅበረ ቅዱሳን በግሉ እንዲጠቀም ወይም በግሉ እንዲከበር ከማሰብ ሳይሆን ማኅበረ ቅዱሳንን ሳስብ እኔ ቤተ ክርስቲያኔን ነው የማስበው። ቤተ ክርስቲያኔን ካላሰብኩ ማኅበረ ቅዱሳንን ማሰብ አልችልም። ማኅበረ ቅዱሳንን አስቤ ቤተ ክርስቲያኔን ማሰብ የምችል ከሆነ ደግሞ ለማኅበረ ቅዱሳን መደረግ የሚገባውን ነገር ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቀውን ሁሉ ማግኘት አለባቸው ብዬ አምናለሁ። በዚሁ ጊዜ ታዲያ አሁን ምናልባት አንዳንድ የሚስተካከሉ ነገሮች ምንድን ናቸው ቢባል አንዳንዶች “ማኅበረ ቅዱሳን” የምትባል ቤተ ክርስቲያን እንደሌላቸው ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። ማኅበሩ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማሳኪያ ይሆን ዘንድ የተመሠረተ እንጂ ራሱ ቤተ ክርስቲያን ይሆን ዘንድ የተቋቋመ አይደለም። ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጐን ትቶ ማኅበሩ ነው ቤተ ክርስቲያን ብሎ የሚያስብ ወጣት ካለ ስህተቱን ሊያርም ያስፈልገዋል። ማኅበረ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰጪ ክፍል ነው፤ የቤተ ክርስቲያን አካል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ማኅበሩን በግልጽ የሚዋጉት አካላት አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ከሚፈጽሙት ተግባር የተለየ አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የሚዘረጉባት የክፋት መረብ ይበቃታል ይህች ቤተ ክርስቲያን። ስለዚህ ልጆቻችንን መሰብሰብ የእኛ ግዴታ፣ የእኛ ኃላፊነት ነው። ምናልባትም ማኅበሩ ተሳስቶ ከመንገድ ከወጣ መቆንጠጥ መቻል አለበት። ሲቆነጠጥ ግን በአግባቡ፣ በመመሪያው እና በሕጉ ሊሆን ይገባል። ይህም ስህተቱን ለማረም እንዲያስችለው ነው። ያለ የሌለውን ስህተት ጨምሮ ማኅበሩን እንደ ጭራቅ አድርጐ ማየቱ እኔ በእውነት አግባብነት ያለው አይመስለኝም። ባለፈው በሚዲያ ሳይቀር የሚተላለፉ ነገሮችን ለማየት ሞክሬአለሁ፣ በእውነቱ ያሳዝነኛል እና እንደዚህ ያሉ ጥቃቅን ነገሮች ሊስተካከሉ የሚገባቸው ናቸው። ነገ ልናገኘው የሚገባንን ጸጋ እንድናገኝ ዛሬ ተባብረን መሥራት ስንችል ነው።

**ሐመረ ኖኅ፡-** በውጪው ዓለም የሚገኘውን ወጣት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣትና በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ሥር ለማቆየት፤ ሕፃናትን በቃለ እግዚአብሔር ኮትኩቶ ለማሳደግ ምን መሠራት አለበት ይላሉ? በእርስዎ ሀገረ ስብከት ምን እየተሠራ ነው?

**ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-** በእኔ ሀገረ ስብከት የተለየ ሥራ አለ ብዬ የምገምተው የለኝም እንደማንኛውም ሀገረ ስብከት እንደማንኛውም አካባቢ በእዚህም ሀገረ ስብከት እየታዩ ያሉ ሙከራዎች ይኖራሉ። ሕፃናትን በአግባቡ ለማስተማር በተለይ የራሳችን የሆነ ቤተ ክርስቲያን የገዛን ክፍሎች ቀጣዩ ትኩረታችን ይህ ስለሆነ ባለን አቅም ሕፃናትን በሥርዓት፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያውቁበት ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት እያደረግን ነው። ይሄ የሚታየው በአጠቃላይ በሀገረ ስብከት ደረጃ ባይሆንም እያንዳንዱ ደብር የሚያሳየው እንቅስቃሴ ግን እንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ነው ያለው።

በሀገረ ስብከት ደረጃ ይህንን ግምገማ ለመስጠት ገና ሀገረ ስብከቱ በጉዞ ላይ ያለ ሀገረ ስብከት ነው። ሀገረ ስብከት ሲባል እኔ እንደለመድኩት ይመስለኝ የነበረው ምንድን ነው ሊቀ ጳጳስ አለ፣ ሥራ አስኪያጅ አለ፣ ጸሐፊ አለ፣ ሌሎችም ሠራተኞች አሉ። እነዚህ ሁሉ የተደራጀ መዋቅር ኖሯቸው አንድ ላይ የሚሰሩ ይመስለኝ ነበር። እንደዚህ ሆኖ ግን አላገኘሁትም። ጳጳሱ ሌላ ስቴት ነው ያሉት፣ ሥራ አስኪያጁ ሌላ ስቴት ነው ያለው፣ ጽሐፊው ሒሳብ ሹሙ ሌላ ሁሉም በየስቴቱ የሚገኙ ናቸው። ሊቀ ጳጳሱ እንግዲህ

በሲኖዶስ በቅዱስ ፓትርያርኩ ተልከው መጥተዋል፤ ባለደሞዝ ናቸው። የተቀሩት ከሥራ አስኪያጅ ጀምሮ እስከ ታች ያሉ አባላት ግን የፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ስለሆነ ገና ሀገረ ስብከቱ በቅጡ የተደራጀ ሀገረ ስብከት አይደለም ለማለት ነው። የሆነ ሆኖ ግን በየአድባራቱ የሚሠሩ ሥራዎች ተስፋ ሰጪ ሥራዎች ናቸው። ከሁሉ በላይ ልጆቻችን ኢትዮጵያዊነታቸውን አውቀው በቤተ ክርስቲያናቸው ሕግና ሥርዓት በአገራቸው ቋንቋ ማወቅ የሚገባቸውን ነገር እንዲያውቁ ጥረት እየተደረገ የሚገኝበት ጊዜ ነው ያለው ብዬ አስባለሁ። በዚሁ መሠረት እንግዲህ ሕፃናትን በቃለ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በብዙ አቅጣጫ ነው ኮትኩቶ ለማሳደግ ጥረት መደረግ ያለበት። ያለንበት ሀገር የባዕድ ሀገር ነው። ልጆቻችን እዚሁ ሲያድጉ የሚረከቡት የባዕዱን ሀገር ባሕል፣ የባዕዱን ሀገር ቋንቋ፣ የባዕዱን ሀገር ሥርዓት እንጂ የራሳቸው ባሕልና ቋንቋ ምን እንደሆነ አያውቁም። እኛ ካልተጋን እኛ ካላስተማርናቸው በጣም ትልቅ ፈተና ሊሆንብን ይችላ ይሄም መሆኑን መነጋገር ያስፈልጋል። ለዚሁ ልዩ ትኩረት ያስፈልገዋል፤ ልዩ ጥናት ያስፈልገዋል። በእውነት ያላወቅነው ብዙ ነገርም እየቀረብን እንዳለ ይሰማኛል።

ስለዚህ ልጆቻችን ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ማወቅ ይገባቸዋል። ልጆቻችን በኢትዮጵያዊ ቋንቋ የሚማሩበት ዕድል ማግኘት አለባቸው። ልጆቻችን ኦርቶዶክሳውያን ሆነው ማደግ የሚችሉበት ነገር መመቻቸት አለበት። ይሄንን ለማድረግ ኅብረቱ ያስፈልጋል። መደማመጡ ያስፈልጋል። እንዲሁ በተለምዶ እንዲህ ብናደርግ ይሳካልናል ብለን የምንለው ነገር አይደለም። ጥናት ያስፈልገዋል። በተለይ ወጣት ልጆቻችን የወጣት ምሁራን አስተዋጽኦ እዚህ ላይ ትልቅ ሚና የሚጫወት ነው መሆን ያለበት ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ በጥናት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት እንድንሰጥ ጥናታቸውን ለእያንዳንዳችን ቢለግሡ ከልጆቻችን ለአገልግሎቱ የሚለግም ማንም የለም። ካለማወቅ የሚቀርብን ብዙ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ለአገልግሎት ግን ሁሉ የተመቻቸ ነገር ሲኖር ሁሉም ለአገልግሎት ማንም የሚለግም ስለሌለ በዚሁ ላይ ብርቱ ሥራ የሚጠብቀን ይመስለኛል። እንደ ሀገር ቤት እንዲሁ በቀላሉ ውላችሁ ግቡ የምንላቸው አይደለም መሆን ያለባቸው ልጆቻችን። ብዙ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ሁኔታ ነው ያለው። አለበለዚያ ግን በገዛ ሀገራቸውና ቤተ ክርስቲያናቸው ባዕዳን ሆነው ነው የሚያድጉት። እኛና ልጆቻችን ሳንተዋወቅ እንቀራለን። ወደፊት አደጋ እንዳያጋጥመን ከወዲሁ ለመከላከል ለመግታት የባለሙያዎች ጥናት ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። ሥራ መሥራት የምንችለው የባለሙያዎች ድጋፍና ጥናት ስናገኝና በጥናት ላይ የተደገፈ ሥራ ስንጀምር ነው ጥሩ ሥራ ሠራን ብለን የምንለው።

***ሐመረ ኖኅ፡-*** በሰሜን አሜሪካ ያለው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ምን ይመስላል? ምንስ መደረግ ይገባዋል?

***ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-*** በእውነቱ እንዲሁ በባዕድ ሀገር ሆነው ሲያዩት አገልግሎቱ ፈቃደ እግዚአብሔር ያለበት ይመስላል። ስደት የሚመረጥ ባይሆንም ነገር ግን መሰደድ ካልቀረ ደግሞ ተሰድዶ ብዙ ችግሮች ላይ መውደቅ አለና ነው። ባሁን በምናየው ግን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሕዝቡ እንደ ሀገር ቤት ሆኖ እየተገለገለ የምናይበት ጊዜ ነው። የትም ስሔድ ልክ ሀገር ቤት እንዳለሁ ሆኖ ነው የሚሰማኝ። አገልግሎቱ የተሟላ ነው። ሕዝቡ ቤተ ክርስቲያን ይወዳል፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል። በተለይ ወጣቱ መንፈሰ እግዚአብሔር እያነሳሳው ቤተ ክርስቲያንን የሚወድበት ጊዜ የሚፈጠሩ አንዳንድ ጥቃቅን ችግሮች እንዳሉ ሆኖ ማለት ነው መንፈሰ እግዚአብሔር እየቀሰቀሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣበት ጊዜ ስለሆነ ያንን ወጣት በቤተ ክርስቲያን ማየቱ፣ አዛውንቱ ሽማግሌው ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው አገልግሎት ሲያገኝ ማየቱ በእውነት አንዳንዴ ባዕድነትን የሚያስረሳ ሁኔታም ይፈጠራል። ስለዚህ ይሄ እግዚአብሔር ፈቅዶ የሚሰጥ አገልግሎት ነውና በዚሁ ይሄ አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ መልካም ይመስለኛል። እስካሁን ድረስ የማየው ግን እርግጥ ሁሉም ተሟልቷል ብዬ ባልልም በባዕድ አገር ነን እስካልን ድረስ ግን ያለው ሁኔታ ሲታይ ተስፋ ሰጪ ጥሩ አገልግሎት እንዳለ ነው የምገነዘበው ለማለት ነው።

ለወደፊት በተለይ የራሳቸው የሆነ ቤተ ክርስቲያን የገዙ ዕዳቸውን እንደ ጨረሱ ቀጣይ ሥራ መሥራት የሚችሉት ምንድን ነው ከተባለም ከሀገር ቤትም የተማሩ ወጣቶችን በማምጣት በያሬዳዊ ዜማ፣ በቅዳሴው ብስለት ያላቸውን መምህራን እያመጡ ልጆቹን ከሥር መኮትኮት፣ ልጆቹን ማሳደግ የሚጠበቅብን ይመስለኛል። ይህንን ካደረግን መሠረት እንጥላለን። ትውልዱን ጽኑ መሠረት እናስይዘዋለን ። ስለዚህ ከጊዜ በኋላ ብዙ ረዥም ነው በማይባል ጊዜ ሥራችን ይሄ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ባለሙያዎችን ከሀገር ቤት በቂ ደሞዝ እየከፈልን ማምጣት ቢቻል በቋሚነት ካልተቻለ ደግሞ በጊዜያዊነት የተወሰነ አገልግሎት እየሰጡ የሚመለሱ ሊቃውንትን ማምጣት ከቻልን ይህንን መሠረት የጸና እናደርገዋለን ብዬ አስባለሁ።

***ሐመረ ኖኅ፡-*** በአባቶች መካከል የተከሰተውን ያለመግባባት በመፍታት ሰላምና አንድነትን ለመፍጠር የተቋቋመው ኮሚቴ አባል መሆንዎ ይታወቃል። ይህን ለማሳካት እስካሁን ምን ሲሠራ ቆይቷል? ምንስ ውጤት ተገኝቷል?

***ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-*** በአጠቃላይ ኮሚቴው በፈቃደ እግዚአብሔር ተነሳስቶ ሥራዎችን ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ጥሩ ጥሩ ሥራዎችን እየሠራ ነው ያለው። በመጀመሪያ ጊዜ ሁላችሁ እንደምትገነዘቡ ለጊዜው መለስተኛ እንቅፋት አጋጥሞን ባይሳካ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተለያዩበት ከ18 ወይም ከ19 ዓመት በኋላ በአንድ አካባቢ እንዲገናኙ በአንድ አካባቢ ለማሰባሰብ እንዲሞክሩ የተደረገበት የታሪክ ሒደት የዚሁ ኮሚቴ ጥረት ውጤት ነበር። ከዚያ በኋላ ያ በሆነ ምክንያት አልተሳካም በዚሁ መሠረት ኮሚቴው ጥረቱን ቀጥሎበታል። በዚሁ ወደ አዲስ አበባ ከሦስት ጊዜ ያላነሰ ልኡካኑን እየላከ አዲስ አበባ ቅዱስ ሲኖዶስ ቅዱስ ፓትሪያርኩን በማግባባት ነገሮች መልክ እንዲያዙ አድርገዋል። እዚህም ላሉ አባቶች መልእክተኞችን እየላከ እንዲሁ ነገሩ እንዲለሳለስ፣ እንዲለዝብ ቤተ ክርስቲያን ከመለያየት እንድትድን የሚደረግበት ሁኔታ እንዲጀመር ለማድረግ ጥረቱን እየቀጠለ ነው ያለው። እርግጠኛ ነኝ መቼም አንድ ቀን እግዚአብሔር ፈቅዶ ሕዝቡ የሚፈልገውን የሚመኘውን የአንድነቱን የምሥራች የሚሰማበት ጊዜ ላይ እንደርሳለን ብለን ነው ተስፋ የምናደርገው። እንግዲህ ለዚህ ደግሞ አንደኛ የሕዝቡ፣ የሊቃውንቱ፣ የካህናቱ ጸሎት ያስፈልገዋል፤ የምዕመናኑ ድጋፍ፣ ጸሎት ያስፈልገዋል። ከሁሉ በላይ ደግሞ እዚህም ያሉም ሆነ እዚያም ያሉ አባቶቻችን የየግሉን ችግር ወደጐን ትተው ለአሐቲ ቤተ ክርስቲያን /ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን/ ኅልውና ለነገይቱ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ታሪክ ማሰብ መቻል አለባቸው። ይሄ ሲሆን ነው ቤተ ክርስቲያን አንዲት የምትሆነው፤ ቤተ ክርስቲያን ሰላም የምትሆነው። ዛሬ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይህ ሰላም እንዳይገኝ ልዩ ልዩ መሰናክሎችን የሚፈጥሩ ክፍሎች እንዳሉ እንገነዘባለን። ይሄ ግን የሚያሳዝን ነገር ነው በእውነቱ። ቤተ ክርስቲያን አንድ ስትሆን ከእግዚአብሔር የሚገኘው በረከት ይገኛል። የቤተ ክርስቲያን አንድነት የአገር አንድነት ጭምር ነው። ይህች ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት የአገር አንድነት ተምሳሌት ሆና የኖረች ቤተ ክርስቲያን በመሆኗ አንድነቷ የአንዱ ወገን ወይም የአንዱ ክፍል ተጠቃሚነትን የሚገልጽ አይደለም። በአጠቃላይ የአገር አንድነት፣

የአገር ሰላምን የሚያረጋግጥ በመሆኑ በሃይማኖት የሚመስሉን በሃይማኖት የማይመስሉን ክፍሎችም ለዚህች ቤተ ክርስቲያን አንድነት ሊያግዙን ከጎናችን ሊቆሙ ይገባል ብዬ አስባለሁ።

ዋናው ነገር ይህችን ቤተ ክርስቲያኑን የማይተው ጠባቂዋ እግዚአብሔር ስላለላት ሰላሙ ይመጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። አሁንም ሒደቱ እንደቀጠለ ነው ያለው። እንዲሁ ተራ ነገር ባለመሆኑ በአንድ ጀምበር ወይም በአንድ ዓመት ውስጥ ለምን ውጤት አልታየም ብለው ከፍላጐታቸው የሚመነጭ ሮሮ የሚያሰሙ ብዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ጥሩ ነው ይሄ ስሜት ጥሩ ነው፤ ክፉ አይደለም። መልካም ነው። ነገር ግን መታወቅ ያለበት ምንድን ነው ጉዳዩ ተራ ነገር አይደለም። ጉዳዩ ቀላል ነገር አይደለም። ይህን ግዙፍ ነገር አስተካክሎ የቤተ ክርስቲያኒቱን አንድነት ለማምጣት የሚጠይቀው ጥረት፣ የሚጠይቀው መሥዋዕትነት ቀላል ባለመሆኑ ትዕግሥት ፣ ጽናት ፣ ጥረት ያስፈልገዋል። ከሁሉ በላይ ደግሞ ጸሎት ያስፈልገዋል። እና እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ምዕመናኑ የዚህችን ቤተ ክርስቲያን የአንድነት የምሥራች የሚሰሙበት ጊዜ ይኖራል ብለን በሙሉ ተስፋ እንጠብቃለን።

**ሐመረ ኖኅ፡-** ለሕዝበ ክርስቲያኑና ለማኅበሩ አባላት የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-** በእውነቱ በመጀመሪያ ከያዝነው ርዕስ አንፃር ለማኅበሩ ልጆች የማስተላልፈው በቅድሚያ ለዋናው ማዕከል የማስተላልፈው በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪም በሚገኙ የማኅበሩ አባላት፣ በማኅበሩ የአገልግሎት ዘርፎች የሚሰጠው አገልግሎት አሁንም እንደበፊቱ፣ እንደቀድሞው የተጠናከረ እንዲሆን፤ ውጤት የሚታይበት፣ ተስፋ የሚጣልበት እንዲሆን ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ ለማለት እፈልጋለሁ። እርግጠኛ ነኝ በቅርብ ጊዜ የተለዩን አባቶች አሉ ማኅበሩን በርቱ አይዟችሁ እያሉ ይመክሩ፣ ቢሳሳት ያርሙ የነበሩ ከማኅበሩ ሲለዩ ማኅበሩ እነዚህን አባቶች ሲያጣ እንዳይዳከም መጠንቀቅ ያስፈልጋል። እነ ሊቀ ጉባኤ አባ አበራን የመሰሉ አባቶች ማኅበሩ ከጐኑ አጥቷል። እነሱ የሚሰጡት አስተዋጽኦ ቀላል አልነበረም። አንደኛ በአባትነታቸው በጸሎታቸውም በበረከታቸውም፤ በሁለተኛ ደረጃ በምኁርነታቸው የሚሰጡት አገልግሎት ቀላል ስላልነበረ እንዲህ እንዲህ ያሉ አባቶች ሲለዩ የሚጓደሉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ እና እነዚያ ነገሮች እንዳይጓደሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል እና በርትታችሁ ሥሩ ለማለት እፈልጋለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ እዚህ ሰሜን አሜሪካም ሆነ በየክፍለ ዓለማቱ ያሉ የማኅበሩ አካላት አሁንም ቢሆን የማኅበሩን መሠረታዊ ዓላማ፣ የማኅበሩን ጥንታዊ ይዘት በትክክል የተገነዘቡ ያወቁ ሆነው አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። በምንም መመዘኛ የእዚህ ማኅበር አገልግሎት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንጂ የግለሰብ አገልግሎት አይደለም መሆን ያለበት። እኔ ዛሬ ማኅበሩን ደግፌ ማኅበሩን ተከትዬ መራመድ እችላለሁ። ጥሩ ነው ድጋፍ መስጠት ተገቢ ነው። ነገር ግን ባልመሰለኝ ጊዜ ደግሞ ከማኅበሩ ዓላማ የወጣ ሥራ በምሠራበት ጊዜ ለእኔ ተብሎ የሚሠራ እስከሌለ ድረስ የእኔን ግድፈት የእኔን ጉድለት ወደ ጐን ትቶ በዓላማ ጽናት አገልግሎት መቀጠል ያስፈልጋል። እኔ እዛው ሀገር ቤት የምናገረውን ደግሜ መናገር እፈልጋለሁ። ማኅበረ ቅዱሳንን የማያውቅ ማኅበረ ቅዱሳን እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ለማኅበሩ ሁሌ የምሰጠው መልእክት ይሄንን ነው። አሁንም እሱን ማጠናከር እፈልጋለሁ፤ ማኅበረ ቅዱሳንን የማያውቅ ማኅበረ ቅዱሳን እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ይሄ ከሆነ አገልግሎቱ ሁሉ የሠመረ ይሆናል። አገልግሎቱ ሁሉ አንድ ይሆናል። ስለዚህ በውጪም በሀገር ቤትም ያሉ ልጆቻችን ወንድሞቻችን እህቶቻችን በዚሁ ዓላማቸውን በግልጽ አውቀው ቀደምት አባሎቻቸው ወንድሞቻቸው የሠሩትን የከፈሉትን መሥዋዕትነት እያስታወሱ መመሪያቸው ሊያደርጉት ይገባል። የቀደሙ ሰዎች አገልግሎት መረሳት የለበትም። እሱ ነው ወደ ቁም ነገር የሚያደርሳቸው። እሱ ነው ወደ እውነት የሚያመጣቸው። የቀደሙ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጥረትና ተጋድሎ የሚረሱ ከሆነ ይሰናከላሉ። ያ እንዳይሆን የቀድሙ በሕይወትም ያሉ የሌሉም ሊኖሩ ይችላሉ እነዚህ የከፈሉትን መሥዋዕትነት የከፈሉትን ዋጋ ማስታወስ ያስፈልጋል። መዘንጋት አያስፈልግም። በእያንዳንዱ በራሱ አንድ ይሄንን የመሰለ ግዙፍ ማኅበር እንዲሁ በነሲብ የተገኘ ነገር አይደለም። እግዚአብሔር ፈቅዶ ነው። ነገር ግን መሥዋዕትነት ተከፍሎበት ብዙ ሰዎች ተጋድለውበት ብዙ ነገር አሳልፈው በትዕግሥትና በተስፋ፣ በጽኑ እምነት ነው ለዚህ የደረሰው እና በዚሁ እንዲቀጥሉ አደራ እላለሁ።

ለሕዝቡ የማስተላልፈው መልእክት ሕዝቡ ቤተ ክርስቲያኑን በትክክል እንዲረዳ እንዲጠብቅ ማድረግ ወቅቱ ነው አሁን። ቀደም ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የነገውን አርቆ ማሰብ ያስፈልጋል። ልጆቻችሁን ጠብቁ እንዲህ አድርጉ ቢባል ዛሬ ልጆች ለወላጆች የሚታዘዙበት ዘመን ሆኖ አይደለም የሚታየው። ግን ወላጆችም ሆኑ ልጆች አንድ እውነታ መገንዘብ አለባቸው ወደ እውነት ለመምጣት። ዛሬ እውነት ነው ስለጠላናቸው አይደለም ወይም ስለማንፈልጋቸው አይደለም የፕሮቴስታንቱ ዓለም መድረሻ ወደሌለበት መንገድ ነው እየተጓዘ ያለው። እየተዘጋ ያለ ድርጅት ነው። ስለዚህ አሁንም ቢሆን እንደው ክርስትና አንድ ነው የሚለውን ፈሊጥ እያመጡ ሕዝቡን የሚያሳስቱን እንዲያውቁባቸው መጠንቀቁ ያስፈልጋል። ከተቻለ ልጆችን መክሮ አስተምሮ ከቤታቸው እንዳይወጡ ወደ ጥፋት እንዳይሔዱ ቤተ ክርስቲያን ለመዝጋት ሩጫ አያስፈልግም። ቤተ ክርስቲያን ለማስፋት ቢሮጥ መልካም ነው። ስለዚህ ከራሳቸው ሕይወት እየተማሩ ሌላውን ከማሰናከል ቢጠነቀቁ የሚያሰናክሉም ሰዎች ይህንን ሰምተው ቢታረሙ መልካም ነው እላለሁ። የቤተ ክርስቲያን ልጆች ደግሞ ቤተሰባቸውን ልጆቻቸውን በጥንቃቄ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲጠብቁ አደራ እንላለን። ፍቅር ሰላም እንዲኖር ያስፈልጋል። ሰላም ከሌለ፣ ፍቅር ከሌለ የክርስትና ትርጉሙ የት እንደሆነም ሊታወቅ አይችልምና ሰላም እንዲኖር፣ ፍቅር እንዲኖር የሁሉም ጥረት ያስፈልጋል። ይሄ ከሆነ እግዚአብሔር በረከቱን ለሀገራችንም ለዓለሙም ሁሉ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር ሁላችንንም በበረከቱ ይጐብኘን።

**ሐመረ ኖኅ፡-** አሜን። ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ጊዜዎን ሰውተው ለጥያቄዎቻችን መልሶች ስለሰጡን፣ ምክርዎንም ስለለገሡን እግዚአብሔር አምላክ ይስጥልን፤ እግዚአብሔር ያክብርልን።

**ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ፡-** እግዚአብሔር ያክብርልኝ። እናንተም አገልግሎታችሁን ያስምር። እግዚአብሔር ሁላችንንም ይጠብቀን። ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ሲል አንድነታችንን ሰላማችንን ይጠብቅልን። አመሰግናለሁ።

**ሐመረ ኖኅ፡-** አሜን።

# ለሕፃናት

## God's Love in Creation

By Dn. Alemayehu Desta

God is the Creator of everything in the universe. There is nothing that was not created by Him. He created the heavens and the earth, angels and mankind, animals and plants… in six days. The first day of creation is Sunday. On the first day, He created the heavens and the earth. On this day also He created light so that we may see. Including Sunday, in six days, God created water so that we may drink and not be thirsty; He created the sun so that it would shine for us during the day and give heat; He created plants that we may eat from their fruit; He created fish in the sea, animals on land, and birds that fly so that we may see the wonders of God and His rule over all creation on earth. Finally, on the Sixth day, on a Friday, He created man in His own image, and He said, "Let them have dominion over the fish of the sea, and over the fowl of the air, and over the cattle, and over all the earth, and over every creeping thing that creeps upon the earth." (Genesis 1:26).



God showed us His love for mankind from the beginning of creation:

- Because God is a loving Father, He prepared everything we need for us before He created Adam and Eve. Loving parents, likewise, prepare everything a child needs before the child is born.
- God created us in His own image and likeness because He wants us to be like Him.
- God created everything simply by speaking. He created light by saying, "Let there be light." He created plants by saying, "Let the earth grow plants." He created all creation except Adam by saying let there be this and that. But He created Adam with His own hands and He breathed on Him to give him life.
- God is the King of the universe. Because He loves us, He made Adam and Eve a king and a queen on earth. When He created them, they had nothing on earth, but He gave them everything on earth to take care of and to rule.

Do you see how our God is such a loving God? God has been showing us His love in many ways since the beginning of creation. How do you show your love for God? There is not anything that we can give Him that is not already His. But we can show our love to God in many different ways. We can show our love by thanking Him for His love, for giving us wonderful parents, and for giving us the house we live in, the clothes we wear, the water we drink, the clean air we breathe. We can also show our love to Him by keeping His commandments through obedience to our parents and showing love to others as He showed us His love. Think of how you can show your love to your brothersስ and sisters, and to your friends.

### የተሳትፎ ጥሪ

የሐመረ ኖኅ ኤሌክትሮኒክስ መጽሔት ዝግጅት ክፍል በኪነ ጥበባት ዓምድ ለሚቀርቡ ጽሑፎች አንባቢያንን ለማሳተፍ አቅዷል። ስለዚህ ዝንባሌና ችሎታው ያለዎ ከሆነ ቢልኩልን በደስታ እንደምንቀበል ልንገልጽ እንወዳለን። የኢ-ሜይል አድራሻችን፡- **mk.edulit@gmail.com**